# የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

# የሦስት ዓመት

# ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

# (2015-2017)

**ነሃሴ፣ 2014 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

ማውጫ

**የሪፖርቱ ጭምቅ (Executive Summary)** ...... 0
**መግቢያ** ...... 3
**ክፍል አንድ ፡ አጠቃላይ** ...... 5
1.1 ...... የጥናቱ አስፈላጊነት ...... 5
**1.2** ...... **የጥናቱ ወሰን** ...... 5
**1.3 የጥናቱ ዘዴ** ...... 5
**1.4 የጥናቱ ውስንነት** ...... 6
**1.5 ከጥናቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች** ...... 6
**ክፍል ሁለት ፡ ስትራቴጂያዊ ትንታኔ** ...... 7
**2.1 የስትራቴጂያዊ ትንታኔ ምንነትና አስፈላጊነት** ...... 7
2.2 በጥናቱ የተካሄዱ ስትራቴጂያዊ ትንተናዎች ...... 7
2.2.1 የማንዴት ትንተና ...... 7
**2.2.2 የውስጣዊና ወጫዊ ሁኔታ ትንተና** ...... 11
2.2.3 አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ...... 18
2.3 የባለድርሻ አካላትን መለየትና ትንተና ...... 19
2.4 የለውጥ አመክኖ ...... 29
2.5 ተልዕኮ እሴቶችና ርዕይ ...... 30
2.5.1 ተልዕኮ ...... 30
**2.5.2 ዕሴቶች** ...... 31
**2.5.3 ርዕይ** ...... 31
**ክፍል ሦስት ፡ ስትራቴጂ** ...... 32
**3.1 ስትራቴጂ** ...... 32
**3.2 የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂያዊ ውጤቶች መግለጫ** ...... 33
**ክፍል አራት ፡ ስትራቴጂያዊ ግቦች መለኪያዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች** ...... 35
**ክፍል አምስት የትግበራ ስልቶች፤** ...... 42
አባሪዎች ...... 47
አባሪ 1፡ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ...... 47
**አባሪ 2 ፡ የስትራቴጂያዊ መለኪያዎች መግለጫ** ...... 56
**አባሪ 3 ፡ የስትራቴጂያዊ እርምጃዎች መግለጫ (የፕሮጀክቶችና በጀት ትስስር)** ...... 63

## ሙዳየ ቃላት

- **ሀገራዊ ምክክር**፡ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ  አዋጅና የኮሚሽኑ ም/ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በሚለዩ አጀንዳዎች ላይ በተለያዩ አካላት ውይይት እንዲደረግባቸው የኮሚሽኑ ምክር ቤት በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የሚያመቻቻቸው ውይይቶች ናቸው ።
- **የኮሚሽኑ ምክር ቤት**፡ ሁሉንም የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮችን በአባልነት ያቀፈ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ነው።
- **ኮሚሽነር**፡ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሰረት በአፈ ጉባዔዉ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ነዉ።
- **አካታችነት፡** ዓይነታቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ብዝሃነት የሚመስል የምክክር ተወካዮችን ማሳተፍና ተሳታፊዎችም በፍትሃዊነትና እኩልነት በምክክር ሂደቱ ማሳተፍን የሚመለከት ነው ።
- **ተልዕኮ፡** የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የመፈጠር ምክንያት ሲሆን የድርጅቱን ዐበይት ተግባራት፣የሚሠራባቸው በታዎችን፣የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች የያዘ አጭር አንቀጽ ነው።
- **ርዕይ፡** የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን  በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚደርስበት የወደፊቱ የተቋሙ ምስል ነው። ርዕይ ፋይዳው የሚለካበት ገዢ ውጤት ያለው ሲሆን የኮሚሽኑ ቅልጥፍናና ውጤታማነት መደምደሚያ የርዕዩ ገዢ ውጤት መሳካት ነው።
- **ገዢ ውጤት፡** ከርዕዩ የሚጠበቀው ውጤት ገዢ ውጤት ይባላል። ገዢ ውጤት አንድ ወይም በብዙ ስትራቴጂዎች ዘመን የሚደረስበት ውጤት ነው። ገዢ ውጤት የኢትዮጵያ  ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለሃገራዊ ራዕይ መሳካት የሚኖረውን አስተዋጽኦ የሚያመለክት ነው።
- **እሴት**፡ የአንድ ተቋም ገዢ ባህሪ ሲሆን በትላልቅ ውሳኔ ወቅት የምንቆምለት መርህ ነው። እሴት የተቋሙ ገዢ ፍልስፍና ወይም እምነት ሲሆን በኮሚሽኑ ደረጃ የሚዘጋጁ እሴቶች ኮር እሴቶች በመባል ይታወቃሉ። ኮር እሴቶች ሁሉንም ቢዝነስ ዩኒቶችንና አካላትን የሚመለከቱ ናቸው።
- **ስትራቴጂ**፡ ራዕያችንን ለማሳካት የምንመርጠው የላቀ መንገድ ነው። ስትራቴጂ ለስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ምላሽ በመስጠት ወይም ስትራቴጂያዊ ተግዳሮቶችን በመፍታት ራዕዩ የሚሳካበት መንገድ ነው።

- **ስትራቴጂያዊ ትንታኔ**፡ ስትራቴጂዊ ትንታኔ ከውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች አንጻር ኮሚሽኑ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል ሳይንሳዊ የምርመራ ጥናት ነው ፡፡
- **ባለድርሻ አካላት፡** የተቋሙ ስኬት ወይም ውድቀት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው አካላት ናቸው፡፡ ባለድርሻ አካላት ዜጎች፣ ለተቋሙ ተግባራት መሳካት አስተዋጾ የሚያደርጉ፣ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ አካላት እና ሌሎች የተቋሙ የተልዕኮ ስኬት የሚመለከታቸውን አካላት ይይዛል፡፡
- **አስቻይ ሁኔታ**፡ አስቻይ ሁኔታ የተቋሙ ጥንካሬና መልካም አጋጣሚ የሚገጣጠሙበት ሁኔታ ነው፡
- **ፈታኝ ሁኔታ**፡ ፈታኝ ሁኔታ የተቋሙ ድክመትና ስጋት የሚገጣጠሙበት ሁኔታ ነው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች**፡ ተቋሙ ራዕዩን ለማሳካት በሚያደርገው ጥረት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ስትራቴጂያዊ ተግዳሮቶች ሲሆኑ ፈታኝ ሁኔታዎች የሚፈጥሩት ተግዳሮቶች ናቸው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ**፡ የተቋሙን ዋና ተግባር የሚገልጹ፣ የትኩረት አቅጣጫን የሚያመልክቱና የስኬት አምድ (**Pillars of Excellence**) ናቸው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ ውጤት፡** ተቋሙ ለይቶ ያስቀመጣቸውን የትኩረት መስኮች በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ሲያደርግ የሚደርስባቸው ውጤቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ አንድ ስትራቴጂያዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡
- **ስትራቴጂያዊ ግብ፡** የተቋሙ ስትራቴጂ የሚገነባባቸው ማዕከሎች ሲሆኑ በስትራቴጂው ዘመን ውስጥ ምን በመስራት ስትራቴጂያዊ ውጤት ላይ እንደርሳለን የሚለውን ጥያቄ የሚመልሱ ናቸው፡
- **ስትራቴጂያዊ መለኪያ፡** የአፈጻፀም መለኪያ በተጠቃለለው የስትራቴጂ ማፕ የተቀመጡ ግቦች የስኬት ደረጃን (ውጤት) ለመመዘን የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡
- **የውጤት መለኪያ (Output measure)**፡ የአገልግሎት ወይም ምርት መጠን መለኪያ ነው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ ዒላማ**፡ ግቡን መሠረት በማድረግ ከተዘጋጀ መለኪያ አኳያ የሚፈለገውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ የአፈጻጸም ደረጃ**፡ ከዒላማው በላይና በታች ወይም ራሱ ዒላማው ሲሳካ ትርጉሙ ምን እንደሆነ የሚያመለክት የአፈጻጸም ውጤት ትርጉም ነው፡፡
- **ስትራቴጂያዊ እርምጃ**፡ በአሁን አፈጻጸምና በዒላማው መካከል የሚኖረውን የአፈጻጸም ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ስትራቴጂያዊ ዒላማዎች የሚሳኩት እርምጃዎች ሲሳኩ ነው፡፡

# የሪፖርቱ ጭምቅ (Executive Summary)


የዚህ ጥናት ዓላማ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በማቋቋሚያው በአዋጅ ቁጥር 1265/2014 የተሰጡትን በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በሚታዩ ልዩነቶች የውይይት አጀንዳዎችን የመለየት፣ ሀገራዊ ምክክር የማካሄድና ምክረ ሃሳብ የማቅረብ ኃላፊነቱን በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለመወጣት የሚያስችለውን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት ነው።

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ለማዘጋጀት በመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ለኮሚሽነሮች የተሰራጩ መጠይቆችና በጽሁፍ የተሰባሰቡ መረጃዎች፣ ከኮሚሽነሮች ጋር በጋራ፣ በንዑስ ቡድንና በተናጠል የተደረጉ ጥልቅ ውይይቶችንና የተለዩ መሠረታዊ አቅጣጫዎችን፣ ኋላም እያንዳንዱ ኮሚሽነር በጽሁፍ የሰጠውን አስተያየት፣ እንዲሁም በረቂቅ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ላይ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ፊት ለፊት የተከናወኑ የአዳራሽ ውይይቶችን ጥናቱ በግባትነት ተጠቅሟል። በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ደግሞ ከባለድርሻ አካላት ጋር ኮሚሽኑ ባደረጋቸው ውይይቶች የተያዙ ቃለ ጉባዔዎችን፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ ቀደም ሲል የኮሚሽነሮች ጉባዔ ያዘጋጀውን ስትራቴጂያዊ ፍኖተ ካርታ፣ የዕቅድ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫና ሌሎች ሰነዶችን፣ በሀገራዊ ምክክር ረገድ የተፃፉ ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔዎችንና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን የያዙ የጽሁፍ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል ።

በመሆኑም ውጫዊ ሁኔታውን ለመረዳት የሚያስችሉ የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮች በጥናቱ ሂደት በጥልቀት ተመርምረዋል።

የውጫዊና የውስጣዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ተደርጎ መልካም አጋጣሚዎች፣ ስጋቶች፣ ጥንካሬዎችና ድክመቶች የተለዩ ሲሆን በኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር አፈጻጸም ዙሪያ ፍላጎት ያላቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ተለይተው በምክክር ሂደቱ ላይ ያላቸው ሚናና የግንዛቤ ደረጃ፣ የሚኖራቸው የተፅዕኖ ደረጃ፣ ለሀገራዊ ምክክሩ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች ተለይተዋል። በውስጣዊና ውጫዊ ትንተና ማጠቃለያም የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ተለይተዋል።

- ሰፊ፣ አካታችና ዓይነተ ብዙ ምክክር በአጭር ጊዜ በውጤታማነት ማከናወን፣
- ጥርጣሬና አለመተማመንን በአጭር ጊዜ በመቀነስ በጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ምክክር ማከናወን፣

- የባለድርሻ አካላትን ፍላጎትና ብቃት አቀናጅቶ መጠቀም፣
- ዓለም አቀፍ ልምዶችን ከአገራዊና አካባቢያዊ የምክክር ልምዶች ጋር አጣጥሞ መጠቀም፣
- የጸጥታ፣ ደህንነት እና የዜጎች መፈናቀል ባሉባቸው አካባቢዎች አካታችና ወካይ ምክክር ማድረግ፣

በመቀጠልም በሥራ ላይ ያለውን የኮሚሽኑ ተልዕኮ ከጥሩ ተልዕኮ ባህሪያት አኳያ የተከለሰ ሲሆን በዚህም መሠረት የኮሚሽኑ ተልዕኮ " **በሀገራችን ኢትዮጵያ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ለተፈጠሩ ልዩነቶችና አለመግባባቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በጥናትና በሕዝባዊ ውይይቶች በመለየት፣ በተለዩ አጀንዳዎች ላይ ሀገራዊ ምክክሮችንና ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ እና ተግባራዊነቱን በመከታተል ለሀገራዊ መግባባት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤**" የሚል ነው።

በተመሳሳይ የኮሚሽኑ ርዕይ ከጥሩ ርዕይ ባህሪያት አኳያ የተከለሰ ሲሆን በዚህም መሠረት አዲሱ ርዕይ "**እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት ተፈጥሮ ማየት**" የሚል ነው፡፡

የኮሚሽኑን ተልዕኮና በአዋጅ የተሰጡትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ዋነኛ ተቋማዊ እሴቶች የተለዩ ሲሆን በዚህም መሠረት የኮሚሽኑ ዋነኛ እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ።

- **አካታችነት**
- **ግልጽነት**
- **ተዓማኒነት**
- **ገለልተኝነት**
- **ምክንያታዊነት እና**
- **አውድ ተኮርነት**

ናቸው።

ተልዕኮ፣ ርዕይና እሴቶችን ለቁልፍ ባለድርሻ አካላት ማጋራት የቀጣይ ዓመታት ቁልፍ የኮሚሽኑ ተግባራት ይሆናሉ።

ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ለመፍታትና ርዕዩን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ሦስት የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂያዊ ውጤቶቻቸው የተለዩ ሲሆን እነርሱም፣

- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 1፡ የላቀ ሀገራዊ ምክክር ሂደት**

  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 1፡ የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት**
- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 2፡ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ትስስርና ብቃት**

  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 2፡ በቂ የቴክኒክ የኃብትና ድጋፍ መገኘት**
- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 3፡ የላቀ የማኅበረሰብ ተሳትፎ፤**

  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 3፡ የህዝብ አመኔታና ቅቡልነት**

ናቸው ።

ስትራቴጂያዊ መስኮቹና ስትራቴጂያዊ ውጤቶቹ የኮሚሽኑ የልህቀት አምዶች የሚያመለክቱ ሲሆን ለአጠቃላይ የኮሚሽኑ ዓላማ ስኬት ማዕቀፍና አቅጣጫ የሚሰጡ ናቸው። የርዕዩም መሳካት በስትራቴጂያዊ ውጤቶቹ መሳካት ላይ የሚመሰረት ይሆናል።

የተሳካ ምክክር በሕዝብ ተሳትፎ ለማከናወን ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራትን የሚጠይቅ ነው። በስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ሥር 11 ግቦች ከነመግለጫቸው፣መለኪያቸው እንዲሁም የአፈፃፀም ዒላማዎች ጋር በዝርዝር ተዘጋጅተው ቀርበዋል።

ስትራቴጂያዊ ግቦቹን ተግባራዊ ለማድረግ 13 ፕሮጀክቶች ተለይተው መግለጫ፣ ይዘት፣ ዋና ዋና የአፈፃጸም ተግባራትና ከግቦቹ ጋር ያላቸው ትስስር፣ ስጋት፣ በጀትና ታሳቢዎች ተዘጋጅተዋል። ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ፕሮጀክቶችም በፕሮግራም መልክ እንዲደራጁ ተደርጓል።

የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስትራቴጂና ዕቅድ በመጨረሻ ክፍል ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

# መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በሚገኙ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነቶች እና አለመግባባቶች በመኖራቸው ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች አማካኝነት ምክክር ተደርጎባቸው ምክረ ሃሳቦች ቀርበው መፍትሄ ማግኘት እንዳለባቸው በመታመኑ ኮሚሽኑ ሊቋቋም ችሏል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአዋጅ ቁጥር 1265/2014 የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ነው። ተቋሙ እንደአስፈላጊነቱ የሚራዘም የሦስት ዓመት ዕድሜ እንደሚኖረው በአዋጁ ተጠቅሷል። ኮሚሽኑ ለሀገራዊ መግባባት ወሳኝ በሆኑ ጭብጦች ላይ ቁልፍ በሆኑ ባለድርሻ አካላት መካከል ውጤታማ ውይይት እንዲደረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያሳልጣል። ኮሚሽኑ በምክክር ከሚያገኛቸው ምክረ ሃሳቦች በመነሳት የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችልና ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያግዙ ምክረ ሃሳቦችን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።

ኮሚሽኑ ገለልተኛ አካል ሲሆን አደረጃጀቱም ፣

- የኮሚሽኑ ምክር ቤት
- ዋና ኮሚሽነር
- ም/ዋና ኮሚሽነር
- ጽ/ቤት
- እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚቴዎች፣ እና
- አስፈላጊ ሠራተኞችን

የሚይዝ ነው።

ኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ለመወጣት ከሚያከናውናቸው የሥራ አመራር ተግባራት አንዱና ቀዳሚው የሦስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀትና ወደ ትግበራ መግባት መተግበር ነው። በዚሁ መሠረት የሪፖርቱ ትኩረት የኮሚሽኑን የቀጣይ ሦስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማመልከት ይሆናል ።

በዚህ ሪፖርት የሚከተሉት ተካተዋል።

- አጠቃላይ ጉዳዮች፣
- ስትራቴጂያዊ ትንታኔዎች፣
- ስትራቴጂዎች፣
- ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች፣ ዒላማዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች፣
- ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፣
- የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስትራቴጂና ዕቅድ፣

ዕቅዱ በኮሚሽኑ ም/ቤት ሲጸድቅ ህጋዊ ሰነድ ሆኖ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

# ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ

## 1.1 የጥናቱ አስፈላጊነት

የሚከተሉት ነጥቦች የጥናቱን አስፈላጊነት በአጭሩ የሚያመለክቱ ናቸው።

- ኮሚሽኑ በህግ የተሰጠውን ማንዴት በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለማስፈጸም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ለመቅረጽ፣
- ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመገምገምና በመረዳት መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀምና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ በቂና አስፈላጊ ስትራቴጂዎችን ለመቅረጽና ለመተግበር፣
- የኮሚሽኑን ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት በጥልቀት በመረዳት የባለድርሻ አካሉን ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል ውስጣዊ ብቃት ለመገንባት፣
- ኮሚሽኑ በሥራ ሂደቱ ሊገጥሙት የሚችሉ ቁልፍ ተግዳሮቶችን በአግባቡ በመረዳት ስትራቴጂያዊ መፍትሄዎችን ለመተግበር ለመስጠት፣
- ተቋማዊ ቅንጅትንና ትስስርን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ተኮር አመራር ለመፍጠር፣
- በስትራቴጂ፣ በፕሮግራሞችና በተቋማዊ ኃብት መካከል ጠንካራ ትስስር በመፍጠር የኮሚሽኑ በጀት ስትራቴጂያዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ እንዲውል የሚያስችል ስትራቴጂያዊ ሥራ አመራር ሥርዓት ለመዘርጋት፣
- በስትራቴጂ፣ በሥራ ሂደቶችና በመዋቅር መካከል ጠንካራ ትስስር በመፍጠር ተቋማዊ ቅልጥፍናና ውጤታማትን ለማረጋገጥ፣ እና
- ተቋማዊ አፈጻጸምን በተጨባጭ መረጃዎች ላይ በመመስረት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት፣

## 1.2 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን የኮሚሽኑን የሦስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት ነው።

## 1.3 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የሚከተሉትን የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ዘዴዎች ሥራ ላይ አውሏል።

- የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ከኮሚሽነሮች ጋር በተደረገ ውይይት አሰባስቧል፤

- የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴን በመጠቀም የኮሚሽኑን ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ውይይት ቃለ ጉባዔዎችን፣ የኮሚሽኑን ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ ጽንሰ ሃሳባዊ ጉዳዮችንና ተሞክሮዎችን የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ጥናቶችን፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ወዘተ.. ጥናቱ በመመርመር ለስትራቴጂው ያላቸውን አንደምታ አንጥሮ አውጥቷል፤
- በረቂቅ ጥናቶች ላይ ከኮሚሽነሮች ጋር ለተከታታይ ጊዜ ውይይት በማድረግ ጥናቱን አዳብሯል፤
- የቁልፍ ባለድርሻ አካላት አውደ ጥናት በማካሄድም ዕቅዱን አጠናክሯል።

## 1.4 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮችን በስፋት ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ጊዜ የተሰጠው አለመሆኑ በእጥረት መልክ የሚታይ ነው። ሆኖም የበሰሉ የጥናት ሥራዎችን በመጠቀም፣ኮሚሽኑ ቀደም ሲል ለልዩ ልዩ ዓላማ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ያሰባሰባቸውን ማስረጃዎች ለዕቅዱ በሚጠቅም አግባብ በግብዓትነት በመጠቀም ለጥናቱ የተሰጠው አነስተኛ ጊዜ ሊያስከትል የሚችለውን ውስንነት በእጅጉ ለመቀነስ ተችሏል።

## 1.5 ከጥናቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች

ከጥናቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ውጤቶች ይጠበቃሉ።

- የሀገሪቱን ዐውድ የሚመጥኑ፣ ነባራዊ እውነታን የሚያንጸባርቁና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ ተልዕኮ፣ እሴቶችና ራዕይ፣
- የችግሮችን ሥረ መሠረት፣ አንደምታና መገለጫዎችን በዝርዝር የሚያሳይ ስትራቴጂያዊ ትንታኔ፣
- የኮሚሽኑን ልህቀትና ቀጣይነት ያለው የአፈጻጸም መሻሻልን የሚያመለክቱ ስትራቴጂዎችና ስትራቴጂያዊ ግቦች፣
- በስታንዳርዱ መሠረት የተዘጋጁ ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች፣ ዒላማዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች፣
- ከስትራቴጂያዊ ግቦች ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ወይም ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፣
- የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ፣
- የተከታታይ ስትራቴጂያዊ ውጤቶች የምክንያትና ውጤት ትስስርንና የለውጥ አመክኖን የሚያሳይ የለውጥ ማዕቀፍ፣
- የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስትራቴጂና ዕቅድ፣

# ክፍል ሁለት፡ ስትራቴጂያዊ ትንታኔ

## 2.1 የስትራቴጂያዊ ትንታኔ ምንነትና አስፈላጊነት

ስትራቴጂያዊ ትንታኔ ማለት የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮችን በመጠቀም ለኮሚሽኑ ስትራቴጂያዊ ፋይዳ ያላቸው መረጃዎች የሚሰበሰቡበት፣ የሚደራጁበትና የሚተነተኑበት እንዲሁም ወሳኝ በሆኑ ነጥቦች ከድምዳሜ ላይ የሚደረስበት የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት መሠረት ነው፡፡ ትንተናው የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ዋነኛ አካል ሲሆን ሳይንሳዊ ግምቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ የአጠቃላይ ጥናቱን ግማሽ ጊዜና ኃብት የሚፈጅ ነው፡፡ የስትራቴጂያዊ ትንተና ፋይዳም ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን መለየትና የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት መረዳት ነው፡፡

### 2.2 በጥናቱ የተካሄዱ ስትራቴጂያዊ ትንተናዎች

#### 2.2.1 የማንዴት ትንተና

የተግባርና ኃላፊነት ትንተና የሚካሄደው የሚከተሉትን ለመረዳት ነው፡፡

- የኮሚሽኑን ዓላማና እሴት ፈጠራ ለመረዳት፣
- ለኮሚሽኑ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ወሰን ለማወቅና የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ወሰን ለመረዳት፣
- ኮሚሽኑ ተልዕኮውን ለመወጣት የሚከተለውን ወይም ሊከተል የሚገባውን አሠራር በዝርዝር ለማወቅ፣ እና
- የኮሚሽኑን ተልዕኮና እሴቶች ይዘት ለመገንዘብ፣

የተግባርና ኃላፊነት ትንታኔ የስትራቴጂያዊ ትንታኔ አንድ አካል ሲሆን ዓላማውም ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ፣ ዋና ዋና ተግባራትንና ልዩ ባህሪውን ለመረዳት ነው፡፡ በዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች ከትንታኔው ለመለየት ያስችላል፡፡

**(ሀ) ኮሚሽኑ የተቋቋመባቸው ተግባርና ኃላፊነቶች፣**

ኮሚሽኑ አሥራ ሦስት የሚሆኑ ተግባርና ኃላፊነቶች የተሰጡት ሲሆን በዝርዝር ሲቀርቡም የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

- ምክክሮችን የሚያመቻቹና የሚያስፈጽሙ፣ የተለያዩ ጥናቶችን የሚያካሂድ እና ምክረ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችን እና የባለሙያ ቡድኖችን ያቋቁማል፤
- ከዚህ በፊት በመንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተደረጉ ሀገራዊ የምክክር ሂደቶችን እና የተገኙ ውጤቶችን ያጠናል፣ በቀጣይ በሚያካሂዳቸውን ሀገራዊ ውይይቶች በግብዓትነት ይጠቀማል፤
- በተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉትን ልዩነቶች በጥናት፣ በሕዝባዊ ውይይቶች ወይም በሌሎች አግባብነት ያላቸውን መንገዶች በመጠቀም ያወያያል፤
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አቀጽ (፫) መሰረት በተገለጹት አጀንዳዎች የለያቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የምክክር አጀንዳዎችን ይቀርጻል፣ ምክክር እንዲደረግባቸው ያመቻቻል፣ ምክክሮችን እና ውይይቶችን ያሳልጣል፤
- ከመላ ሀገሪቱ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እና አካላትን የሚወክሉ ተሳታፊዎች የሚሳተፉባቸው፣ ሀገራዊ መግባባት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ የምክክር ስብሰባዎችን በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲካሄዱ ያመቻቻል፤
- በሀገራዊ የምክክር ጉባዔ ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን ግልፅ በሆኑ መስፈርቶች እና የአሠራር ሥርዓት መሠረት ያወያያል፣ በምክክሮች ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፤ ይህን የተመለተከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤
- ምክክሮቹ በኮሚሽነሮች ወይም የኮሚሽነሮች ምክር ቤት በሚሰይማቸው አወያዮች አማካኝነት እንዲመሩ ያደርጋል፤ በአወያይነት የሚመድባቸዉ ሰዎችም በተቻለ መጠን በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፫ ላይ የተመለከቱትን ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤
- በምክክር ሂደቶች የሚደረጉ ምክክሮችን ቃለ ጉባዔ የሚይዙ፣ የቀረቡ ምክረ ሃሳቦችን የሚያጠናቅሩ እና አደራጅተው ለኮሚሽነሮች ምክር ቤት የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን ይመድባል፤
- የጽህፈት ቤቱን የውስጥ የአሠራር ሥርዓት፣ የምክክር አጀንዳዎች ወይም አርዕስት የሚመረጡበትን የሚመለከት፣ በሀገራዊ ውይይቶች ላይ የሚሳተፉ አካላት የሚወያዩበትን ሥርዓት በመዘርጋትና መሰል ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ውስጠ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

- የሀገራዊ ምክክር ጉባዔ አጀንዳዎችን፣ የምክክሮቹን ሂደት፣ በምክክሮቹ የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን እንዲሁም ምክረ ሃሳቦቹ በተግባር ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሥልት የሚገልጽ ሰነድ በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለአስፈፃሚ አካሉ እና ለሌሎች ለሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ያቀርባል፤ ለሕዝብም ይፋ ያደርጋል፤
- መንግሥት ከሀገራዊ ውይይቶች የሚገኙ ምክረ ሃሳቦችን በተግባር ላይ ለማዋል እንዲችል ግልፅ እና ተጨባጭ የሆነ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤
- የምክረ ሃሳቦቹን አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

በመሆኑም የኮሚሽኑ ተልዕኮ ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራትና ኃላፊነቶች አጠቃሎ የሚይዝና ወሰኑም በተግባርና ኃላፊነቱ ዙሪያ ይሆናል ሊሆን ይገባዋል።

ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል ለኮሚሽኑ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ቁልፍ ተግባርና ኃላፊነቶች ወደ ሥራ ሂደትነት ሲመነዘሩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

- **የቅድመ ዝግጅትና ዝግጅት ተግባራት -** ጽ/ቤቱን ማደራጀትና የተለያዩ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፣ መሠረታዊ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና አካላት ተሳታፊዎችን መለየት፣ አጀንዳዎችን በጥናትና በህዝባዊ ውይይቶች መለየት፣
- **በአጀንዳዎች ላይ የማወያየት ሂደት -** በአጀንዳዎች ላይ የሚከናወኑ ውይይቶችን ማመቻቸትና የውይይት ውጤቶችን መዝግቦ መያዝ፣
- **ምክረ ሃሳቦችን መቀመርና የትግበራ ዕቅድ ማዘጋጀት -** ምክረ ሃሳቦችን በመቀመር ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤትና ለህዝብ ማቅረብ፣ መንግስት ምክረ ሃሳቦችን የሚተገብርበትን ዕቅድ እንዲያዘጋጅ እገዛ ማድረግ፣
- **የምክረ ሃሳቦችን አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት -** ምክረ ሃሳቦችን ለመተግበር የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣

### (ለ) የኮሚሽኑ አደረጃጀት

ቀደም ሲል በመግቢያው እንደተገለጸው ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሲሆን በሚከተለው አግባብ የተደራጀ ነው።

- የኮሚሽኑ ምክር ቤት
- ዋና ኮሚሽነር
- ም/ዋና ኮሚሽነር
- ጽ/ቤት
- እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚቴዎች፣ እና
- አስፈላጊ ሠራተኞች

**(ሐ) የኮሚሽኑ ላዕላይ አደረጃጀት ባህሪ ለስትራቴጂያዊ ዕቅድ የሚኖረው አንድምታ፣**

- ኮሚሽኑ ተግባሩን በመደበኛና በኮሚቴ አደረጃጀት አማካይነት የሚያከናውን ከመሆኑም በላይ የተሰጠው ዕድሜ በአንፃራዊነት አጭር መሆኑ ለዚሁ የሚመጥኑ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንደሚኖሩት ታሳቢ ያደርጋል፤
- የፋይናንስ አስተዳደርንና ሌሎች ተግባራትን በነጻነትና በገለልተኝነት የሚያከናውን መሆኑ ዕቅዱ ቀላልና ተለማጭ እንዲሆን ያስችለዋል፤
- ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ መደበኛ እና የፕሮግራም / የፕሮጀክት ሥራዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ሊሆን ይገባል፤

**(መ) ተግባርና ኃላፊነቱ ለተልዕኮና እሴት ቀረጻ የሚኖረው አንደምታ፣**

ከማንዴቱ ለተልዕኮው ግብዓት የሚሆኑት የሚከተሉት ናቸው ፡፡

የኮሚሽኑ ተግባራት ከቁልፍ የውጤት መስኮች ወይም የትኩረት መስኮች ጋር ያላቸው ትስስር፣

**የኮሚሽኑ ኮር ሂደት “ምክክር ማካሄድ” ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ፣**

- የምክክር ተሳታፊዎችን በየደረጃው መለየት፣
- አወያዮችንና ሰብሳቢዎችን በየደረጃው መለየት፣
- የምክክር አጀንዳዎችን ማሰባሰብና መቅረጽ፣
- ውይይቶችን ማደራጀት፣ ማመቻቸትና ማስፈጸም፣
- ምክረ ሃሳቦችን ማጠናቀር፣ እና
- የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣

ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ነጥቦች በተልዕኮ መግለጫው አካል የሚሆኑ ናቸው።

### 2.2.2 የጥንካሬ ድክመት፤ የመልካም አጋጣሚ ስጋት ትንተና

የጥንካሬ ድክመት፤ የመልካም አጋጣሚ ስጋት ትንተና የተካሄደው የኮሚሽኑን ስትራቴጂያዊ ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም መልካም አጋጣሚ ስጋት ለመለየትና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን አንጥሮ ለማውጣት ነው፡

**(ሀ) ውስጣዊ ሁኔታ - ውስጣዊ ተግዳሮቶች**

ኮሚሽኑ አዲስ የተቋቋመ መንግስታዊ መስሪያ ቤት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን እንደነባር መስሪያ ቤቶች ድርጅት ድክመቶቹንና ጥንካሬዎቹን በቀጥታ ብሎ መተንተን አስቸጋሪ

በመሆኑና ተጨባጭም ባለመሆኑ ኮሚሽኑ የተፈጠሩለትን ብቃቶችና የሚኖሩበትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች በውስጣዊ ትንታኔ መመልከቱ ተገቢ አካሄድ ሆኖ ተገኝቷል፤

**ሠንጠረዥ 1፡ የኮሚሽኑ ውስጣዊ ብቃቶችና ተግዳሮቶች**

| ውስጣዊ ብቃት | ውስጣዊ ተግዳሮቶች |
| --- | --- |
| ▪ ኮሚሽኑ ለህግ አውጭው አካል ተጠሪና ገለልተኛ ሆኖ ከመቋቋሙም በላይ ግልጽና የተሟላ ተግባርና ኃላፊነት (ማንዴት) እንዲሁም ላዕላይ መዋቅራዊ ቅርጽ በህግ የተሰጠው መሆኑ፣<br>▪ የኮሚሽነሮች ም/ቤት ተገቢነት ያለው የሙያ ስብጥር ባላቸውና ተልዕኳቸውን በተረዱ ኮሚሽነሮች የተደራጀ መሆኑ ለተቋማዊ ውጤታማነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>▪ ኮሚሽኑ በዋነኛነት ሀገሪቱ በመደበችው በጀት የሚተዳደር መሆኑ፣ | ▪ ለሀገራዊ ምክክር የሚፈለገውን ብቃትና ኃብት በአጭር ጊዜ አሰባስቦና አደራጅቶ መጠቀም መቻል፣<br>▪ በአጭር ጊዜ ርዕዩንና ስትራቴጂውን ለቁልፍ ባለድርሻ አካላት በማጋራትና ህዝባዊ ንቅናቄ በመፍጠር ሂደቱን በተቋማዊ ግለት መምራት፣<br>▪ ቀጣይነት ያለው ውጤት ተኮር የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በማከናወን የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የኮሚሽኑን ተዓማኒነትና ተቀባይነት በሚፈለገው ደረጃ ማጠናከር፣<br>▪ ራሱን ተደራሽ ለማድረግና ተቀባይነቱን ለማሳደግ የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸውና ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ የሚያስከትሉ የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ሳያሰልሱ ማከናወን፣<br>▪ ኢኮቴን በስፋትና በብቃት በመጠቀም የምክክርን ሽፋን ማሳደግና ሂደቱን ተደራሽ ማድረግ፣<br>▪ ከተለዋዋጭ ሀገራዊ እና የአገሪቱና ዓለምአቀፋዊ የዓለም ሁኔታዎች ፈጥኖ በመማር ወቅታዊ ተግዳሮቶችን መቋቋምና ስኬታማ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ፣<br>▪ የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ማከናወን፤ |

### (ለ) መልካም አጋጣሚና ስጋቶች (ውጫዊ ሁኔታ)

የውጫዊ ሁኔታ ትንተና የሚከናወነው መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን ለመለየት ሲሆን ትንተናውም የተከናወነው ውጫዊ ሁኔታውን በሚያመለክቱ ስድስት መስፈርቶች አማካይነት ነው፡፡

- **ፖለቲካ**: ከሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) አንጻር ዓለም የተሳሰረች በመሆኑ ዓለም አቀፍ ፖለቲካ በአገር አቀፍ ፖለቲካ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ የአገር ውስጥ ፖለቲካም  በአገር  ውስጥ ሰላምና ልማትን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱ የሆነ ሚና ያለው ከመሆኑም ባሻገር ዓለም አቀፍ አንደምታም አለው። ይህ ትስስር በአሁኑ ወቅት የጎላ ነው፡፡

  ፖለቲካ በዓለም አቀፍ የጥቅሞች ትስስር የሚመራና በሰጥቶ መቀበል መርህ የሚተዳደር ሂደት ነው፡፡ ሰጥቶ የመቀበሉ ጨዋታ ጫዎታ የሚመሠረተው በአገሮች የመስጠትና መቀበል አቅም ነው፡፡ የሌላውን ፍላጎት መረዳትና የአገር ውስጥ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች የእነማንን ጥቅም እንደሚነኩና ጥቅማችን ተነክቷል ብለው የሚያምኑ አገሮችና አካላት ምን ዓይነት አጸፋዊ እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ መገንዘብን ይጠይቃል፡፡
- **ኢኮኖሚ**፡ ኢኮኖሚ የፖለቲካ ሥርዓቱ ነጸብራቅ ሲሆን በታወቁ የኢኮኖሚ ጤንነት መለኪያዎች የአገር ውስጥ ኢኮኖሚውን በዓለም አቀፍ ትስስር የሚደርሰበትን ጫና እና ጭምር ከዚህም ጫና የሚከሰቱ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን ያያል፡፡
- **ማህበራዊ ሁኔታ**፡ ማህበራዊ ሁኔታዎች ከህዝብ ቁጥር መብዛት አንጻር፣ ከባህልና አስተሳሰብ፣ ከሥራ አጥነትና ከዲሞግራፊ፣ ከትምህርትና ጤና ሁኔታዎች አንጻር ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን ይመለከታል፡፡
- **ቴክኖሎጂ፡** በአገራዊ ምክክር ሂደት የቴክኖሎጂ ጠቀሜታንና የቴክኖሎጂ ደህንነት ስጋትን የሚመለከት ነው፡፡ ቴክኖሎጂው የሚሰጠውን መልካም አጋጣሚና ስጋት ከምክክር ሂደቱ አንጻር በጥልቀት ያያል፡፡ ቴክኖሎጂ ሲባል የቴክኖሎጂ ኢንፍራስትራክቸርን፣ ሶፍትዌርንና የሰው ኃይል የቴክኖሎጂ የመጠቀም ጉጉትና ብቃትን የሚመለከት ነው፡፡
- **አካባቢያዊ ሁኔታ**፡ አካባቢያዊ ሁኔታ የአካባቢ ብክለትና በረሃማነት የሚያስከትሉትን ስጋትና በሌላ በኩል የአረንጓዴ ልማት የሚሰጠውን መልካም አጋጣሚ የሚመለከት ነው።
- **ህጋዊ ሁኔታ፡** ልዩ ልዩ የአገሪቱ የህግ ማዕቀፎችና አገሪቱ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች የሚሰጡትን መልካም አጋጣሚና ስጋቶች የሚመለከት ነው፤

ውጫዊ ሁኔታውን፡-

- ዓለም አቀፋዊ፣
- አህጉራዊ፣
- ቀጠናዊ፣
- ሀገራዊ፣
- አካባቢያዊ/ክልላዊ

ምህዳሮች አኳያ በትንተናው ተመላክቷል ይመለከታል።

ከዚህም በተጨማሪ በየመስፈርቶቹ የተመለከቱ ጭብጦች የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ናቸው።

- **ስትራቴጂያዊ መሆናቸው፡-** በተለይ የኮሚሽኑን ዋና ኮር የሥራ ሂደቶች አፈጻጸምን የሚወስኑ ጉዳዮች መሆናቸውና ሁለንተናዊ፣ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸው፤
- **የክስተቶችን አዝማሚያን (trend) የሚያሳዩ መሆናቸው፡-** ክስተቶቹ ቢያንስ ባለፉት ሦስት ዓመታት የተዘወተሩ መሆናቸው፤
- **በአሁኑ ጊዜ በኮሚሽኑ የዕሴት ፈጠራ ሂደት እንቅፋት የሆኑ ወይም ዕድል የፈጠሩ መሆናቸውም ታይቷል።**

በውጫዊ ትንተና ለማየት የተሞከረው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክርን ከማሳካት አንጻር የኮሚሽኑ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው።

**ሠንጠረዥ 2፣ የመልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተና**

| መስፈርት | መልካም አጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|
| **ፖለቲካ** | ▪ ሀገሪቱ ዘመናትን የተሻገረ የመንግስት ሥርዓት ያላት እንደመሆኑ መጠን ጠንካራ መንግስት በመፍጠር ያጋጠሟትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ሰፊ ተሞክሮ ያላት መሆኑ፣<br>▪ የኢትዮጵያ ህዝብ የተሳሰረና የተጋመደ ማንነት ያለው በመሆኑ በነጠላ ማንነት ለመከፋፈል የማይመች መሆኑ፣ | ▪ የጋራ ሀገራዊ ርዕይ በሚፈለገው ደረጃ አለመጋራቱ፣<br>▪ ችግሮችን በአመጽና በትጥቅ ትግል የመፍታት ፍላጎት እየጎለበተ መምጣትና አመጽን በአገሪቱ በማስፋፋት ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም የሚሹ የውጭ ኃይላት ከመቼውም ጊዜ በላይ መበራከታቸው፣<br>▪ የዳበረ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት አለመኖር፣<br>▪ መሠረታዊ በሆኑ የአገሪቱ የታሪክ ትርክቶች ላይ የጋራ መግባባት አለመፈጠሩ ለግጭቶች መስፋፋትና ለፖለቲካ አለመረጋጋት መነሻ መሆኑ፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | ▪ የታሪኳ የስኬት ዘመኖች ችግሮቿን ለመፍታትና ግዙፍ ህዝባዊ ርዕይ ለመያዝ አነቃቂ መሆናቸው፣<br>▪ ህገ መንግስቱ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በግልጽና በተሟላ መልኩ የያዘ መሆኑ ለሀገራዊ ምክክር ህጋዊነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>▪ ሀገሪቱ የምትገኝበት የጸጥታ ችግርና የፖለቲካ አለመረጋጋት ላይ የህዝቡ ሰላም ወዳድነትና ናፋቂነት ሲደመር የሀገራዊ ምክክርንና መግባባትን አስፈላጊነትና ወቅታዊነት ግድ የሚያደርገው መሆኑ፣ | ▪ በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የተፈናቃይ ቁጥር መጨመሩ አካታች ምክክር ለማከናወን ፈታኝ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>▪ ሀገሪቱ በምትገኝበት ጂኦ ፖለቲካ ምክንያት የውጭ ሀገራት ጣልቃ ገብነት እያደገ መምጣቱና ጎረቤት አገሮች በውስጥ ችግራቸው የሚናጡ መሆኑ የውስጥ ችግራቸውን ለማስተንፈስና የሦስተኛ ወገን ፍላጎት በማስፈጸም ትኩረትን ለማግኘት ሲሉ በጎረቤት አገሮች ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ መሆኑ፣ |
| **ኢኮኖሚ** | ▪ ሀገሪቱ ሊለማ የሚችል ዓይነተ ብዙና ሰፊ የተፈጥሮ ኃብት ያላት መሆኑ፣<br>▪ ለግሉን ሴክተር ዕድል የሚሰጥ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ መነደፉና ውጤትም እያስገኘ መሆኑ፣<br>▪ ድህነትን ማሸነፍ የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ አጀንዳ መሆኑ፣ | ▪ ኢኮኖሚው ዝቅተኛ ምርታማነት ላይ የሚገኝ መሆኑና በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊና አዋጭ በሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ እሴት በመጨመር የዋጋ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ረገድ የሚፈለገው ብቃት ያልዳበረ መሆኑ፣<br>▪ በዋጋ መናርና በዜጎች የመግዛት አቅም መዳከም ምክንያት ከፍተኛ የኑሮ ውድነት መከሰቱ፣<br>▪ ዓለም ዓቀፍ የገንዘብና የኢኮኖሚ ቀውስ መከሰት፣ |
| **ማህበራዊ** | ▪ ጥንታዊና ባህላዊ አማራጭ የግጭት መፍቻ ስልቶች መኖራቸው፣<br>▪ ከፍተኛ የወጣቶች ቁጥር መኖር፣<br>▪ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች የውይይት ባህል እንዲዳብር መድረኮችን መፍጠራቸው፣<br>▪ የሲቪክ ማህበራት ነጻነት እያደገ መምጣቱ፣ | ▪ የሥራ ባህል በሚፈለገው ደረጃ ያልዳበረ መሆኑ፣<br>▪ በመረጃና በዕውቀት የታነጸ ህብረተሰብ ባለመፈጠሩ ምክንያት በሃሳብ ፉክክር የሚያምነው የህብረተሰብ ቁጥር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>▪ የትምህርት ጥራትና አግባብነት እያሽቆለቆለ ከመምጣቱም በላይ የትምህርት ሥርዓቱ በስነ ምግባር ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ባህል ላይ የማይሠራ በመሆኑ ተቀራርቦ ለመወያየትና ለመመካከር ምቹ ሁኔታ ያልፈጠረ መሆኑ፣<br>▪ ተቋማዊነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣<br>▪ ሙስና መስፋፋቱ የህዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ምክክር ለማድረግና ስምምነት ላይ ለመድረስ እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ▪ ገዢ የሆነው የማህበረሰቡ የአስተሳሰብ ውቅር በአሸናፊነትና ተሸናፊነት ላይ የተመሠረተ እንጂ በሚዛናዊነት፣ በአዳማጭነትና በጋራ አሸናፊነት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ብዝሃ አስተሳሰብንና ምክንያታዊ የሃሳብ የበላይነትን በበቂ ሁኔታ የማያስተናግድ መሆኑ፣<br>▪ የሚዲያ ነጻነትና የሙያ ሥነ ምግባር በሚፈለገው ደረጃ ያልዳበረ በመሆኑ አንዳንድ ሚዲያዎች በስሜትና የየቡድኑን ጥቅም በማስቀደም የሚሠሩ በመሆኑ ለአድሎና ለግጭት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ መሆኑ፣<br>▪ በህዝቡ እምነት የሚጣልባቸው የሲቪክ ማህበራት በሚፈለገው መጠን ጥራትና ተደራሽነት አለመኖር የህዝቡን ህያው ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣<br>▪ ዝምታንና በጉዳዮች ዙሪያ ገለልተኛነትን የሚመርጠው ህዝብ ቁጥር ከፍተኛ መሆን በምክክር ሂደቱ የህዝቡን ንቁ ተሳትፎንና ባለቤትነት ማረጋገጥ አዳጋች መሆኑ፣<br>▪ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል የአንዳንድ ፖለቲካ ድርጅቶች ድጋፍና ከኮሚሽኑ ጋር ተባብሮ ለመሥራት ያላቸው አመኔታ፣ ፈቃደኝነትና ዝግጁነት ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>▪ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ከኢኮኖሚው አጠቃላይ ምርታማነት ምጣኔ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑ፣<br>▪ በባህላዊ ምክክርና ሽምግልና ስርዓት ሥራ በአብዛኛው/በዋናነት አባታዊ ሥርዓቱ የበላይነት ያለው በመሆኑ የሴቶችን ተሳትፎ ሊቀንሰው የሚችል መሆኑ፣ (የአውራምባ)<br>▪ የሲቪል ማህበረሰቡ በሀገራዊ ምክክር ስልትና አመራር ረገድ በቂ ልምድና ተሞክሮ የሌላቸው መሆኑ፣ |
| **ቴክኖሎጂ** | ▪ ለምክክር ሥራ የሚያግዙ እንደ ቪዲዮ ኮንፈርንሲንግ፣ መተግበሪያዎች፣ የትርጉም መሳሪያዎች፣ ወዘተ.. የመሳሰሉ ተደራሽነትን የሚያሰፉ አማራጭ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) መኖራቸው፣<br>▪ የሀገራዊ ምክክር ባህልን ሊያጎለብቱና አካባቢያዊ የግጭት አፈታት ስልቶችን | ▪ የሀገሪቱ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኢንፍራስትራክቸርና ኔትወርክ ደካማ መሆን የቴክኖሎጂና የምክክር ተደራሽነትን ውስን የሚያደርግ መሆኑ፣<br>▪ መሠረታዊ የኢኮቴ ዕውቀትና ግንዛቤ ያለው የህዝብ ቁጥር ብዛት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | ለመጠቀም የሚረዱ የመረጃ ልውውጥ ቴክኖሎጂዎች እያደጉ መምጣታቸው፣<br>▪ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የማስፋፋት ሥራ እያደገ መምጣቱ ተግባራዊ መደረጉ፣ | ▪ የማህራዊ ሚዲያን በመጠቀም ማህበረሰባዊ ግጭቶች እንዲከሰቱ የሚያደርጉ እና የተከሰቱትንም የሚያባብሱና በተጋነነና በተሳሳተ መንገድ የሚዘግቡ የሀሰት መረጃዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸው፣ |
| **አካባቢ** | ▪ የአካባቢ ጥበቃና አረንዴ ልማት ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ መምጣቱ፣<br>▪ በሀገሪቱ ግሪን ኢኮኖሚ / የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ሥራን እንደ ባህል ለመገንባት ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች ባሳተፈ መልኩ ንቅናቄ መጀመሩ፣ | ▪ የህዝብ ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ መጨመሩ በተፈጥሮ ኃብትና አካባቢ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ጫና እያደገ መሄድ ለግጭትና ለኃብት ሽሚያ በር የሚከፍት በመሆኑ ሀገራዊ መግባባትን ሊጎዳ መቻሉ፣<br>▪ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ድርቅ፣ ረሃብ፣ ወዘተ እንዲስፋፉ የሚያደርግ በመሆኑ ለዜጎች መፈናቀልና ግጭት አንዱና ዋንኛው መንስዔ መሆኑ፣<br>▪ የዓለም ሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት መዛበት እያስከተለው ያለው ዓለም አቀፍ ጥፋት የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ጫና የአገራችንን ሰላምና ደህንነት የሚፈታተን መሆኑ፣ |
| **ህግ** | ▪ በቂና ሊያሠራ የሚችል የህግ ማዕቀፍ መኖር፣<br>▪ የፍትህ ዘርፉን ለማሻሻል በመከናወን ላይ ያሉ የሪፎርም ሥራዎች መኖራቸው፣ | ▪ የፍትህ አካላት በቅንጅት የማይሠሩ ከመሆናቸውም በላይ የፍርድ ቤቶች ተደራሽነትና ቅልጥፍና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ የፍርድ ውሳኔ ተፈጻሚነት ጎታታና አሰልቺ መሆኑ፣<br>▪ በህግ አውጭው፣ ህግ ተርጓሚውና አስፈጻሚው መካከል ቁጥጥርና ሚዛንን የመጠበቅ አሠራር የጎለበተ አለመሆኑ የህግ የበላይነት እንዲዳከም የሚያደርግ በመሆኑ መቀራረብን፣ መተማመንንና መግባባትን የሚሸረሸር መሆኑ፣ |

### 2.2.3 አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች

**(ሀ) አስቻይ ሁኔታዎች፤**

- በቂና ሊያሰሩ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች መኖር፣
- ዘርፈ ብዙ ሙያ ባላቸው ገለልተኛ ኮሚሽነሮች እና የኮሚሽነሮች ምክር ቤት መደራጀቱ፤
- የጎለበተ ጥንታዊና ባህላዊ የምክክር ሂደትና የዕርቅ ሥርዓት ያለው አገር ከመሆኑም በላይ ሃገራዊ ምክክርን በተመለከተ በቂ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ መኖሩ፤
- ሀገሪቱ የምትገኝበት የፀጥታ ችግር ሀገራዊ ምክክርን አስፈላጊ ያደረገው መሆኑና ምክክሩን በነጻና ገለልተኛ አካል ለማከናወን የመንግስት ቁርጠኝነት መኖሩ፤
- የምክክር ሂደቱ አስፈላጊነትና ወቅታዊነት ላይ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ መደረሱና የቴክኒክና የበጀት ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ለማግኘት የሚያስችሉ ዕድሎች መፈጠራቸው፤

**(ለ) ፈታኝ ሁኔታዎች፤**

- ዘመናዊና ባህላዊ የሀገራዊ ምክክር ልምዶችን አጣጥሞ የመጠቀም ብቃት፣
- በሂደቱ ላይ አንዳንድ ልሂቃንና የፖለቲካ መሪዎች ያላቸው ጥርጣሬ ያልተፈታ መሆኑ፤
- የማንነት ፉክክርና የታሪክ ሽሚያ እያደገ መሄድ በሀሳብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ምክክር ለማድረግ አዳጋች መሆኑና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሚዲያዎች ግላዊና ቡድናዊ ጥቅምን በማስቀደም የሚሰሩ በመሆኑ ለአድልዎና ለግጭት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለምክክር ሂደቱ እንቅፋት የሚፈጥሩ መሆኑ፤
- ሁሉንም አካታች በሆነ መልኩ ምክክሩን ለማከናወን የፀጥታና የደህንነት ስጋት በስፋት ከመኖሩም በላይ አማራጭ የግንኙነት መስመር ለመዘርጋት በኮሚሽኑ ያሉ ተቋማዊ መሠረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ ያልጎለበቱ መሆናቸው፤
- በመረጃና በዕውቀት የታነፀ ሕብረተሰብ አለመፈጠሩ ላልተረጋገጠ መረጃና ለተዛባ ትርክት በቀላሉ የሚጋለጥ በመሆኑ ለምክክሩ ሂደት እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ ታውቆ ችግሩን የሚያቃልል ውጤታማና ቀልጣፋ የትምህርት፣ ኢንፎሜሽንና ኮሙኒኬሽን ፕሮግራም አለመዘርጋቱ፤

### 2.2.4 ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች፤

- ሰፊ፣ አካታችና ዓይነተ ብዙ ምክክር በአጭር ጊዜ በቅልጥፍናና በውጤታማነት ማከናወን፣

- ጥርጣሬና አለመተማመንን በአጭር ጊዜ በመቀነስ በጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ምክክር ማከናወን፣
- የባለድርሻ አካላትን ፍላጎትና ብቃት አቀናጅቶ መጠቀም፣
- ዓለም አቀፍ ልምዶችን ከአገራዊና አካባቢያዊ የምክክር ልምዶች ጋር አጣጥሞ መጠቀም፣
- የጸጥታ፣ ደህንነት እና የዜጎች መፈናቀል ባሉባቸው አካባቢዎች አካታችና ወካይ ምክክር ማድረግ፣
- የምክክር ምክረ ሃሳቦች በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

## 2.3 የባለድርሻ አካላትን መለየትና ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል የኮሚሽኑ ባለድርሻ አካላት ይለያሉ፤ የባለድርሻ አካላቱ የተጽዕኖና የፍላጎት ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮችን መሠረት በማድረግ ይመለከታል። ባለድርሻ አካል ማለት የኮሚሽኑ ተልዕኮ መሳካት የሚመለከተው አካል ሲሆን በተጽዕኖ ብርታታቸውና በፍላጎት ደረጃቸው ቁልፍና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተብለውም ይለያሉ። የትንታኔው ዋነኛ ግቦችም ባለድርሻ አካላትን መለየትና በተጽእኖና በፍላጎት ደረጃቸው ቁልፍ የሆኑትን ማመልከትና ባለድርሻ አካላቱ ከኮሚሽኑ የሚፈልጉትንና ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላቱ የሚፈልገውን በግልጽ በማመልከት ትብብርንና ትግግዝን ማዳበር ነው።

ሠንጠረዥ፡ 3 የባለድርሻ አካላት ትንታኔ

| ተ/ቁ | ባለድርሻ አካል | ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካሉ የሚጠብቀው | የባለድርሻ አካሉ ፍላጎት | ፍላጎታቸው ባይሟላ የሚያስከተለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖና ፍላጎት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግለሰብ / ዜጋ | ▪ ለኮሚሽኑ መረጃዎችንና ግብረ መልሶችን በወቅቱ መስጠት፣<br>▪ የሀገራዊ ምክክር ግንባር ቀደም ተሳታፊና ባለቤት መሆን፣<br>▪ በምክክር ስብሰባዎች የመሳተፍ ዕድል የማያገኙ ዜጎች ሃሳባቸውን በሌላ መንገድ ለኮሚሽኑ መስጠት፣ | ▪ ሀገራዊ ውይይቱ ግልጽ፣ አሳታፊ፣ አካታችና ከተጽዕኖ የተላቀቀ እንዲሆን፣<br>▪ ዜጋው ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጣቸው አጀንዳዎች ላይ ሀገራዊ ውይይቱ ትኩረቱን እንዲያደርግ፣<br>▪ ስምምነት የተደረሰባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ተግባራዊ ሆነው ሀገራዊ ሰላምና መረጋጋት እንዲረጋገጥ፣ | ▪ በኮሚሽኑ ላይ እምነት ማጣትና የተሳትፎ መቀነስ፣<br>▪ የአጀንዳዎች ትክክለኛነት፣ ጥራትና አግባብነት አለመረጋገጥ፣<br>▪ የውሳኔዎች አለመተግበር፣<br>▪ ሰላምና መረጋጋት አለመስፈን፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 2 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | ▪ የሕግ ማዕቀፍ ማፅደቅ፤<br>▪ ዕቅድና በቂ በጀት በወቅቱ ማፅደቅ፤<br>▪ የሕግ አውጪ አካል በመሆኑ ወሳኝ በሆኑና ሕጋዊ ቅርፅና ይዘት ለሚገባቸው ጉዳዮች ፈጣን ምላሽ መስጠት፤<br>▪ በምክክር ሂደቱ የተለዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣<br>▪ ልዩ ልዩ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና | ▪ ኮሚሽኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ሲወጣ ማየት፣<br>▪ ኮሚሽኑ ስለአፈጻጸሙ በየወቅቱ የተሟላ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብ ፣<br>▪ በጀትን በአግባቡ መጠቀም፣<br>▪ ከማንኛውም አካል ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ መሥራት፣<br>▪ ም/ቤቱ ለሚሰጠው ግብረ መልስ ወቅታዊ ምላሽ መስጠት፣ | ▪ ህጋዊ ተጠያቂነት፣<br>▪ የም/ቤቱ ወሳኝ ድጋፎች መቀነስ፣<br>▪ የኮሚሽኑ ገጽታ መበላሸት፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እንዲወጡ ሚዛናዊ ቁጥጥር ማድረግ፤<br>▪ በምክክር ሂደቱ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ያልተወጡ የመንግስት መ/ቤቶችን ተጠያቂ ማድረግ፣<br>▪ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና<br>▪ ወቅታዊ ምላሽ መስጠት፣ | | | |
| 3 | የፖለቲካ ፓርቲዎች | ▪ ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ የሚያስችል የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣<br>▪ ግልጽነትና ተጠያቂነት፣<br>▪ ለሂደቱ ፖለቲካዊ ድጋፍ መስጠትና በሂደቱ ውስጥ እየተሳተፉ ጉድለቶች እንዲሞሉ አስተያየት መስጠትና እገዛ ማድረግ፣<br>▪ በሂደቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ | ▪ ግልጽነትና ገለልተኝነት፣<br>▪ በቂና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፣<br>▪ በቁልፍ ጉዳዮች ላይ መመካከር፣<br>▪ የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር መከላከል፣<br>▪ ከፓርቲዎቹ ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ፣<br>▪ የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ ድጋፍ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይኖረው በጥንቃቄ ማየት፣<br>▪ | ▪ ገጽታ መበላሸት፣<br>▪ ተከታዮቻቸው በሂደቱ እንዳይሳተፉ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፣<br>▪ ህዝቡ በምክክር ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዳይኖረው ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፣<br>▪ በተመረጡ አጀንዳዎች ላይ ስምምነትና መግባባት እንዳይደረስ ሊያደናቅፉ ይችላሉ፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 4 | አስፈጻሚ አካላት/ የመንግስት መ/ቤቶች | ▪ ትብብር፣ ትግግዝና ቅንጅታዊ አሠራር፣<br>▪ የዕውቀትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣<br>▪ የበጀት አቅርቦት፣<br>▪ የሎጂስቲክስ ድጋፍ፣ | ▪ ወቅታዊ መረጃ መስጠት<br>▪ በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ ህጋዊ ግንኙነት መመስረት፣<br>▪ የማይጣሱ ሀገራዊ የኃብት አስተዳደር ህጎችን አክብሮ መሥራት፣<br>▪ የኃብት አጠቃቀም ውጤታማነት፣ | ▪ የትብብርና ትግግዝ መቀነስ፣<br>▪ የኃብት አጠቃቀም አፈጻጸም መዳከም፣<br>▪ የቅንጅታዊ አሠራር መዳከም፣<br>▪ የአሠራር ክፍተት መፈጠር፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ግንኙነቶች ድጋፍ፣<br>▪ ለምክክር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ | | | |
| 5 | የክልል / የከተማ አስተዳደር ም/ ቤቶች | ▪ በየክልሉ / ከተማ አስተዳደሩ ለሚደረጉ ምክክሮች ድጋፍ መስጠት፣<br>▪ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የምክክር አሠራር እንዲዘረጋ ማገዝ፣<br>▪ የኮሚሽኑን ወቅታዊ ተደራሽነት ማሳለጥ /ማስፋት፣<br>▪ እንደአስፈላጊነቱ ቢሮዎችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለኮሚሽኑ ማቅረብ፣ | ▪ የክልላቸው / ከተማ አስተዳደራቸው ልዩ ጉዳይ የሀገራዊ ምክክር አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፣<br>▪ የክልሉ / የከተማው ህዝብ እኩል ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ ነጥረው የወጡ ምክረ ሃሳቦች ላይ መረጃ መስጠት፣<br>▪ በትግበራ ወቅት የሚኖራቸውን ሚና ማወቅ፣ | ▪ ኮሚሽኑ ከክልሉ/ ከተማ አስተዳደሩ ተገቢውን ድጋፍ አያገኝም፣<br>▪ በምክክር ሃሳቡ ነጥረው የወጡና በአካባቢው ሊተገበሩ የሚገባቸው ምክረ ሃሳቦች ላይተገበሩ ይችላሉ፤<br>▪ ምክረ ሃሳቦች አውድ ተኮር ላይሆኑ ይችላሉ፤ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 6 | የፍትህ አካላት | ▪ በምክክር ሂደቱ በንቃት መሳተፍ፣<br>▪ ለምክክር ሂደቱ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣ | ▪ ፍትሃዊ ምክክር መካሄዱ፣<br>▪ የህግ የበላይነትን ያከበረ ሀገራዊ ምክክር መካሄዱ፣ | ▪ የህግ መጣስ ሊደርስ ይችላል፤<br>▪ የፍትህ መዘግየት ሊያጋጥም ይችላል፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ.<br>▪ ከፍተኛ<br>▪ ከፍተኛ፣ |
| 7 | ሀገራዊ ልሂቃን | ▪ በሀገራዊ ውይይቶች በቅንነት መሳተፍ፣<br>▪ ኮሚሽኑን በላቸው ዕውቀትና ተቀባይነት ማገዝ፣<br>▪ የአጀንዳዎች ተደራሽነትን ማገዝ፣ | ▪ ግልጽ፣ አሳታፊና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ አሠራር፣<br>▪ ምክንያታዊ የምክክር አሠራር መኖር፣ | ▪ ኮሚሽኑ ያገኘውን ጥሩ ገጽታ ወደ መጥፎ ገጽታ ለመቀየር ሊሠሩ ይችላሉ፤<br>▪ ለኮሚሽኑ የሚሰጡት ሁለንተናዊ እገዛ ሊቀንስ ይችላል ይቀንሳል፤ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ በምክክሩ ሂደት ላይ ገንቢ ሚና መጫወት፣ | | ▪ የህዝቡ ተሰትፎ ሊቀንስ ይችላል ይቀንሳል፤ | |
| 8 | የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች | ▪ በምክክር ሂደቱ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ትብብርና ተሳትፎ፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ ጥንቃቄ የሚሹ የሰብዓዊ መብቶችን መረዳት፣ | ▪ በምክክር ሂደቱ የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣<br>▪ ይበልጥ ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በምክክር ሂደቱ እንዲሳተፉ መደረጉ፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ቢያጋጥም ምርመራ ማድረግ፣ | ▪ የኮሚሽኑ ተዓማኒነት መቀነስ፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 9 | አገር አቀፍ የሲቪክ ማኅበራት | ▪ የማህበሩ አመራርና አባላት ንቁ ተሳትፎ፣<br>▪ ከማህበራቱ አመራርና አባላት ጋር ምክክር ማድረግ፣<br>▪ ማህበራቱ በተቀናጀ መልኩ መሳተፍ፣<br>▪ የዕውቀት፣ ቴክኒክና ክህሎት ድጋፍ ማድረግ፣<br>▪ ለአባሎቻቸው የቅስቀሳና ግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መስራት፣<br>▪ በኮሚሽኑና በህዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ረገድ አዎንታዊ ሚና መጫወት፣ | ▪ በቂና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ የሚወክሏቸው አባላት በነጻነት መሳተፍ፣<br>▪ ሂደቱ አሳታፊና አካታች መሆኑ፣<br>▪ የሴቶች ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ መጎልበት፣<br>▪ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ በንቃት መሳተፍ፣<br>▪ ፍትሃዊ ውክልና እንዲኖራቸው ማስቻል፣ | ▪ የንቅናቄ መቀዛቀዝ፣<br>▪ ሂደቱ ተዓማኒነት ማጣትና የገጽታ መበላሸት፣<br>▪ ወቅታዊና አንገብጋቢ አጀንዳዎች በጥልቀት እንዳይታዩ ሊያደርጉ ይችላል፤<br>▪ በቂ ውክልና ከሌላቸው ሂደቱን ሊያደናቅፉ ይችላሉ፣ | ▪ መካከለኛ ተጽእኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 10 | የሚዲያ ተቋማት | ▪ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን በዜና | ▪ በቂና ትክክለኛ መረጃ መስጠት፣ | ▪ የመረጃ መዛባትና ጎዶሎ መሆን፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ፕሮግራም በሁነቶች እና መግለጫዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ለህዝቡ ተደራሽ ማድረግ፣<br>▪ ከኮሚሽኑ ጋር በመርህ ላይ በተመሠረተ ትብብር መሥራት፣<br>▪ ህዝባዊ ንቃት ምክክር መፍጠር፣<br>▪ ህዝቡ በኮሚሽኑ ላይ አመኔታው እንዲጎለብት ማድረግ፣ | ▪ በሀገራዊ ምክክር የሚዲያ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት፣<br>▪ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ግንኙነት መፍጠር፣ | ▪ የህዝብ አመኔታ መቀነስ፣<br>▪ የህዝብ ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ አለመጎልበት፣<br>▪ የህዝብ ንቅናቄ በሚፈለገው ደረጃ አለመዳበር፣ | |
| 11 | የሰላምና ፀጥታ መዋቅር (ፌዴራል፣ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ) | ▪ በውይይት መድረኮች ጸጥታን ማስከበር፣<br>▪ የተሳታፊዎችን ደህንነት ማረጋገጥ፣<br>▪ ጠንካራ ትብብርና ቅንጅታዊ አሠራር መኖር፣<br>▪ የኮሚሽነሮችና የኮሚሽኑን ሠራተኞች ደህንነት መጠበቅ፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ በንቃት መሳተፍ፣ | ▪ ስለውይይት መድረኮች ጊዜ ቦታና የተሳታፊዎች ማንነት ላይ በቂ መረጃ መስጠት፣<br>▪ የተሳታፊዎች ሚናና ኃላፊነትን ማሳወቅ፣<br>▪ የኮሚሽኑን መመሪያዎች በማህበረሰብ ደረጃ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፣<br>▪ | ▪ ሰላምና ጸጥታ መደፍረስና የሂደቱ መደናቀፍ፣<br>▪ የተሳታፊዎች ደህንነት አደጋ ላይ መውደቅ፣<br>▪ የኮሚሽነሮችና የኮሚሽኑ ሠራተኞች ደህንነት አደጋ ላይ መውደቅ፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 12 | ወጣቶች | ▪ ከላዕላይ እስከ ማህበረሰባዊ መዋቅር ያሉ ወጣቶች በሂደቱ በንቃት እንዲሳተፉ፣ | ▪ በምክክር ሂደቱ ትርጉም ባለው ሁኔታ ተሳታፊነታቸውን ማረጋገጥ፣<br>▪ ውክልናቸው መረጋገጡ፣ | ▪ ተሳትፎ መቀነስ<br>▪ የምክክር ሂደቱ የወጣቶች ፍላጎት በአግባቡ ባለመንጸባረቁ ወጣቶች ወደ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ ፍላጎታቸውን በአግባቡ እንዲያንፀባርቁ፣<br>▪ በኮሚሽኑ ውስጥ በተለያዩ ተግባራት ላይ መሳተፍ፣ | ▪ ሂደቱ ወጣቶችንም ማካተቱ፣ ውክልናቸው መረጋገጡ፣<br>▪ ሂደቱ ወጣቶችንም ማካተቱ፣ | ግጭትና ሁከት ሊገቡ ይችላሉ፤<br>▪ ወጣቶችን የሚመለከቱ ቁልፍ አጀንዳዎች ምላሽ ሳያገኙ ሊቀሩ ይችላሉ፣<br>▪ ወጣቶች ለማህበራዊ ቀውስ ስለሚጋለጡ ምክክሩ ፋይዳ ቢስ ሊሆን ይችላል፤ | |
| 13 | የትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋማት | ▪ በጥናትና ምርምር አጀንዳ መለየት ሥራ ላይ መሳተፍ፣<br>▪ የማማከር አገልግሎት መስጠት፣<br>▪ በኮሚሽኑ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የሥልጠና አገልግሎት መስጠት፣<br>▪ በኮንፍረንሶች ዝግጅት መሳተፍ፣<br>▪ በሀገራዊ ምክክር ምሁራዊ የውይይት መድኮችን ማመቻቸት፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ፣ | ▪ የተሳትፎ ዕድል መስጠት፣<br>▪ በሚከናወኑ ጥናቶችና ምርምሮች ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠት፣<br>▪ ለጥናትና ምርምር በጀት መመደብ፣<br>▪ የጋራ ምክክር መድረኮች መፍጠር፣ | ▪ ጥናትና ምርምር በሚፈለገው ጥራትና በበቂ ሁኔታ አለመከናወን፣<br>▪ በጥናት ላይ የተመሠረተ የመፍትሄ ሃሳብ እጥረት መከሰትና በዚህም ብዥታ መኖሩ፣ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |
| 14 | የልማት አጋሮች | ▪ የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣<br>▪ የምክክር ሂደቱ በዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ ተቀባይነት | ▪ በታወቀ አሠራር መመራት፣<br>▪ መሠረቱ ሰፊ የሆነ ምክክር ማካሄድ፣ | ▪ የሚፈለገው የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ ይቀንሳል፣<br>▪ የኮሚሽኑ ዓለም አቀፍ ገጽታ ይዳከማል፣ | ▪ መካከለኛ ተፅዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እንዲያገኝ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ መስጠት፣ | ▪ አካታችና አሳታፊ የምክክር ሂደት መተግበር፣<br>▪ ዓለም አቀፍ ልምዶችን መጠቀም፣<br>▪ የልማት አጋሮች በሂደቱ የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ማሳወቅ፣<br>▪ የጂኦ ፖለቲካውን ሁኔታ ያገናዘበ የምክክር ሂደት ማከናወን፣<br>▪ የጋራ ስምምነቶች አፈጻጸም ላይ ክትትል ማድረግ፣ | | |
| 15 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | ▪ በህብረተሰቡ የውክልና ጉዳዮች ላይ ልምድ ማካፈል፣<br>▪ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ልምድ ማካፈል፣ | ▪ ዜጋው በአግባቡ የሚወከልበት የምክክር ሥርዓት እንዲዘረጋ፣<br>▪ | ▪ አጋርነቱን ይቀንሳል፤ | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |
| 16 | ሴቶች | ▪ በምክክር ሂደቱ ከላዕላይ እስከ ማህበረሰባዊ መዋቅር ያሉ ሴቶች በሂደቱ እንዲካተቱና በንቃት እንዲሳተፉ፣<br>▪ ከሚሽኑ ውስጥ የተለያየ ተግባራት ላይ መሳተፍ፣ | ▪ በምክክር ሂደቱ ትርጉም ባለው ሁኔታ ተሳታፊነታቸውን ማረጋገጥ፣<br>▪ ውክልናቸው መረጋገጡ፣<br>▪ ለውይይት የሚመረጡ አጀንዳዎች የሴቶችን ጉዳይንም እንዲይዙ መደረጉ፣<br>▪ ሴቶች ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሥልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ማግኘት፣ | ▪ ተሳትፎ መቀነስ<br>▪ ሴቶች ለማህበራዊ ቀውስ ስለሚጋለጡ ምክክሩ ፋይዳ ቢስ ሊሆን ይችላል፤ | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |
| 17 | የጤና / አካል ጉዳተኞች | ▪ በምክክር ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ | ▪ የምክክር ሂደቱ የዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽንን መሠረት ባደረገ መልኩ መካሄዱ (ለምሳሌ ያህልም፣ | ▪ የአካል ጉዳተኞች ውክልናና ተሳትፎ መቀነስ፣ | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ ከፍተኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በአግባቡ በምክክር አጀንዳዎች እንዲካተት፣<br>▪ ፍትሃዊ ውክልና ማግኘት፣<br>▪ በኮሚሽኑ ውስጥ በተለያዩ ተግባራት ላይ መሳተፍ፣ | ኢትዮጵያዊ የምልክት ቋንቋ፣ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ የስብሰባ ቦታ፣ ልዩ ድጋፍና እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ፣ ወዘተ)<br>▪ የመሳተፊያ መመሪያ እንዲዘጋጅላቸው መደረጉ፣ | ▪ የምክክር አጀንዳዎችና ምክረ ሃሳቦች አካል ጉዳተኞችን የማያካተት ሊሆን ይችላል፤ | |
| 18 | ሀገራዊ ሽምግልና ላይ የሚሠሩ ዜጎች | ▪ ባህላዊ የምክክር ልምዶችን እንዲያካፍሉ፣<br>▪ በማህበረሰቡ ያላቸውን ተሰሚነት መሠረት ያደረገ የቅስቀሳ ሥራ እንዲሠሩ፣<br>▪ በምክክር ሂደቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣<br>▪ አማራጭ አካባቢያዊ የመፍትሄ ሃሳቦችን እንዲያመላክቱ፣ | ▪ የምክክር ሂደቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ፣<br>▪ የተሳትፎ ሂደቱ የይስሙላ እንዳይሆን ጥንቃቄ እንዲደረግ፣ | ▪ ተሳትፎ መቀነስ<br>▪ ተቀባይነትና አመኔታ ማጣት | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |
| 19 | የኃይማኖት መሪዎች | ▪ ተከታዮቻቸው በሂደቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስተማር፣ ማሳመንና መገሰጽ፣<br>▪ መሪዎቹ በምክክር ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ | ▪ እውነተኛ ምክክር እንዲሆን፣<br>▪ ውይይቶች ሥነ ምግባራዊ አካሄድን በጠበቀ መልኩ እንዲካሄዱ ተጽዕኖ ማሳደር፣<br>▪ | ▪ ተዓማኒነት መቀነስ፣<br>▪ ተሳትፎ መቀነስ፣ | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |
| 20 | የኢትዮጵያ ዲያስፖራ | ▪ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣<br>▪ የዓለም ምርጥ ተሞክሮን ማካፈል፣ | ▪ በኢትዮጵያ ሰላም የሚያመጣ ሀገራዊ ምክክር መካሄዱ፣<br>▪ የሀገራዊ ምክክር ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ መሆናቸው፣ | ▪ ተዓማኒነት መቀነስ፣<br>▪ ድጋፍ መቀነስ | ▪ ከፍተኛ ተጽእኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ ዲያስፖራው በሀገራዊ ምክክርና ተያያዥ ጉዳዮች ያለውን ኔትወርክ መጠቀም፣<br>▪ ዜግነታቸውን ያልቀየሩ ዲያስፖራዎች በሂደቱ እንደዜጋ መሳተፍ፣ | ▪ በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ተቀባይነት ያለው ሀገራዊ ምክክር መከናወኑ፣ | | |
| 21 | የንግድ ማህበረሰብ | ▪ የንግዱ ማህበረሰብ በምክክር ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው እንዲያደርጉ፣<br>▪ የመንግስትና የግሉ ሴክተር ምክክር ተሞክሮን እንዲያካፍሉ፣<br>▪ በየዘርፋቸው ከምክክር ሂደቱ ጋር የተያያዙ ጥናቶችን እንዲያካፍሉ፣ | ▪ የንግዱ ማህበረሰብን በቀጥታ ያሳተፈ ምክክር እንዲካሄድ ይፈልጋሉ፣<br>▪ የንግዱ ማህበረሰብ ህብረተሰብ መሠረታዊ ጉዳዮች የምክክር አጀንዳ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ፤<br>▪ የምክክሩ ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ ሆነው የንግዱ ዘርፍ ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ይፈልጋሉ፤ | ▪ የንግዱ ማህበረሰብ በሂደቱ እንዳይሳተፍ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፤ | ▪ ከፍተኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |
| 22 | የሙያ ማህበራት | ▪ በጥናትና ምርምር ሙያዊ እገዛ፣<br>▪ አባሎቻቸው በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፣<br>▪ በየሙያው ዲሲፕሊን የምክክር ሂደቱን ማገዝ፣<br>▪ አባሎቻቸው ሙያዊ ሥነ ምግባራቸውን አክብረው በሂደቱ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ | ▪ አባሎቻቸው በእኩልነትና በአካታችነት በምክክር ሂደቱ እንዲሳተፉ እንዲደረግ፣<br>▪ ልዩ ሙያን በሚጠይቁ ጉዳዮች ምክር እንዲጠየቁ ይፈልጋሉ፣<br>▪ የምክክር መደምደሚያዎች በሳይንሳዊ ጥናትም የተደገፉ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ፣ | ▪ አባሎቻቸው በሂደቱ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሳተፉ ሊያደርጉ ይችላሉ፤<br>▪ የምክክር ሂደቱን ታማኝነትና ቅቡልነት የሚጎዳ አስተያየት ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ | ▪ መካከለኛ ተጽዕኖ<br>▪ መካከለኛ ፍላጎት |

## 2.4 የለውጥ አመክኖ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ፋይዳ** | ዘላቂነት ያለው ልዩነትን በውይይትና በምክክር የመፍታት ባህል መጎልበት፤ | ▪ አስተማማኝ ሰላም የሰፈነበት የፖለቲካና ማኅበራዊ መደላድል መፈጠር፣<br>▪ ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግስት መፈጠር፣ | የዳበረ ማኅበራዊ መተማመንና ተቀራርቦ የመስራት ባህል መሠረት መጣል፣ | **እሳቤዎች፡**<br>▪ በሂደቱ ውስጥ ቀጣይነት ያለው የሕዝብ ድጋፍና እገዛና/ ባለቤትነት መረጋገጥና፤<br>▪ የፖለቲካ ቁጠኝነት መጎልበት፣ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ስኬት** | በሚመለከታቸው አካላት ተቀባይነት ያገኙ ምክረ ሃሳቦችና ምክረ ሃሳቦቹን ተግባራዊ ለማድረግ የተፈጠረ ተቋማዊ አቅምና የአሠራር ሥርዓት | ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ በመሆናቸው ምክንያት የተፈቱ ወቅታዊ ችግሮች | በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች የተፈጠረ መግባባት | ተመልሰው በመገንበት ላይ ያሉ ማኅበራዊ እሴቶች | **እሳቤዎች፡**<br>• ሰላም ፀጥታና ደህንነት እየተሻሻለ መምጣት፤<br>• የመንግስት ቁርጠኝት እየጎበተ መሄድ፣<br>• የፖለቲካ ልሂቃን በሂደቱ ላይ እምነት በማሳደራቸው ምክንያት ለምክረ ሃሳቦች ተግባራዊነት የሚኖራቸው ድጋፍና አዎንታዊ አስተዋፅዖ እየተጠናከ ይሄዳል፤ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ውጤት** | በህዝብ ምክክር የተለዩ የምክክር አከንዳዎች | የተከናወኑ ቀልጣፋና ውጤታማ የሕዝብ ምክክር መድረኮች | ስምምነትና መግባባት ላይ የተደረሰባቸው በቂና ወሳኝ አጀንዳዎች | ተግባራዊ እንዲሆኑ የቀረቡ ምክረ ሃሳቦች | **እሳቤዎች፤**<br>• ሰፊ የህዝብ ተሳትፎና ተቀባይነት ይኖራል፤<br>• የሴክሬታሪያቱ ፅ/ቤት ብቃትና ቁርጠኝነት እየተጠናከረ ይመጣል፤<br>• አወያዮችና አመቻቾች ሚናቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፤ |

## 2.5 ተልዕኮ፣ እሴቶችና ርዕይ

የተልዕኮ እሴቶችና ርዕይ ቀረጻ የሚከተሉትን መሠረት ያደርጋል።

- የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት፣
- በሥራ ላይ የሚገኙ የኮሚሽኑ ተልዕኮ፣ እሴቶችና ርዕይ፣
- የጥሩ ተልዕኮ እሴቶችና ርዕይ ባህሪያት፣

### 2.5.1 ተልዕኮ

የጥሩ ተልዕኮ ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው።

- የተቋሙን ማንነትና ለምን ዓላማና እነማንን ለማገልግል እንደተቋቋመ የሚያሳይ፤
- የተቋሙን የመፈጠር ምክንያት የሚገልጽ፤
- የተቋሙን ባህሪያት (የሚያቀርበውን አገልግሎት/ምርት፣ የሚያገለግለውን ኅብረተሰብ/ ገበያ፣ የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት እና ልዩ መገለጫው)፣ እና
- በምጣኔው ከአንድ አንቀጽ / ቢበዛ ከሦስት መስመር የማይበልጥ፤

በመሆኑም ቀደም ሲል ከተከናወነው ማንዴት ትንተና በመነሳትና የጥሩ ተልዕኮ ባህሪያትን በማገናዘብ የሚከተለው ተልዕኮ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

**<u>ተልዕኮ</u>**

**በሀገራችን ኢትዮጵያ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ለተፈጠሩ ልዩነቶችና አለመግባባቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በጥናትና በሕዝባዊ ውይይቶች በመሰብሰብ፣ በተለዩ አጀንዳዎች ላይ ሀገራዊ ምክክሮችን በማካሄድ፣ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ እና ለተግባራዊነቱም የመከታተያ ስርዓት በመዘርጋት ለሀገራዊ መግባባት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤**

### 2.5.2 ዕሴቶች

ዕሴቶች በባህሪያቸው የተልዕኮ ኦፕሬሽን መርሆዎች ሲሆኑ ጥሩ የሚባሉ ዕሴቶች የሚከተሉት ባህሪያት ይኖሯቸዋል፡፡

- ከተቋሙ ተልዕኮ አንጻር ለየትኞቹ መርሆዎች መቆም እንዳለብን የሚያሳዩ መሆናቸው፣
- የተቋሙ ማህበረሰብ ሊጋራቸው የሚገቡ ስነ ምግባሮችንና ሌሎች ባህሪያትን የያዙ መሆናቸው፣
- የህብረተሰቡን አዎንታዊ እሴቶች የሚያንጸባርቁ መሆናቸው፣
- ሰዋዊ መሆናቸው፣
- ለቀን ተቀን ምግባራችንና ለውሳኔ አሰጣጣችን ስነ ምግባራዊ አቅጣጫ የሚያሳዩ መሆናቸው፣ እና
- ከተቋሙ ተልዕኮ፣ ርዕይና አዎንታዊ ባህሎች ጋር የተቀናጁ መሆናቸው፣

የኮሚሽኑ ተቋማዊ እሴቶች ኮሚሽኑ የተቋቋመባቸውን መርሆዎች፣ የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት፣ ዓለም አቀፍና አገራዊ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **አካታችነት**
- **ግልጽነት**
- **ተዓማኒነት**
- **ገለልተኝነት**
- **ምክንያታዊነት**
- **አውድ ተኮርነት**
- **አጋርነትና ትብብር**
- **ቅልጥፍናና ውጤታማነት**

### 2.5.3 ርዕይ

የጥሩ ርዕይ ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ከአገሪቱ ርዕይ ጋር ያለውን ትስስር የሚያሳይ፣
- ተቋሙ በስትራቴጂዊ ዘመኑ የት መድረስ እንደሚፈልግ የሚያሳይ፣
- የተቋሙን የወደፊት ፍላጎትና ምስል የሚያሳይ፣

- አጭር / ከአንድ መስመር የማይበልጥ፣ ለመረዳትና ለማስረዳት ቀላል የሆነ፣
- ሊለካ የሚችል፣ ተጨማሪ አቅም ለመገንበት የሚያስችል፣ የተንጠራራ ግብ በውስጡ የያዘ ወይም ለይቶ ከርዕዩ በተናጠል ያስቀመጠ፣
- ባለድርሻ አካላትን ሁሉ የማነሳሳትና  የማነቃነቅ  ብቃት ያለው፣
- የተቋሙን ልዩ ባህሪ (Niche) የሚያመለክት፣

የኮሚሽኑ ርዕይ ሲቀረጽ የቁልፍ ባለድርሻ አካላት አስተያየት ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት የሚከተለው የኮሚሽኑ ርዕይ ሆኖ ተቀርጿል።

**እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት ተፈጥሮ ማየት።**

ከርዕዩ የሚጠበቁ ውጤቶችም የሚከተሉት ናቸው።

- አስተማማኝ ሰላም ለመፍጠርና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችል ማህበራዊ ውል፤
- ዘላቂነት ያለውና የዳበረ ልዩነትን በውይይትና በምክክር የመፍታት ባህል፤
- ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግስት መፈጠር፣

# ክፍል ሦስት፡ ስትራቴጂ

በዚህ ክፍል ቀደም ሲል የተለዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ለመፍታት፣ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ለማረጋገጥና የኮሚሽኑን ተልዕኮ እና ርዕይ ወደ ኦፐሬሽን ለመለወጥ የሚያስችሉ ሦስት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ወይም የስትራቴጂው ምሰሶዎች ተለይተው ቀርበዋል። በእያንዳንዱ የትኩረት መስክም ሊፈጸሙ የሚገባቸው ስትራቴጂያዊ ግቦችም ተዘጋጅተዋል። የግቦች ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች፣ ዒላማዎች እና የአፈጻጸም ደረጃዎችን ተካተው ቀርበዋል ።

## 3.1 ስትራቴጂ

ስትራቴጂ በተለያዩ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዕቀፎች የተለያዩ ስያሜዎች የሚሰጡት ሲሆን ዋነኞቹ ስትራቴጂያዊ **የትኩረት መስክ (Strategic Focus Areas)፣ቁልፍ የውጤት አመልካች (Key Result Areas) እና ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች (Goals)** በመባል ይታወቃሉ። በዚህ ሰነድ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ የሚለው ነው ።

ከስትራቴጂያዊው ትንታኔ በመነሳት የሚከተሉት ሦስት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና የትኩረት መስኮች ሲከናወኑ የሚገኙ ስትራቴጂያዊ ውጤቶች ተለይተዋል ።

- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 1፡ የላቀ ሀገራዊ ምክክር**
  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 1፡ የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት**
- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 2፡ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ትስስርና ብቃት**
  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 2፡ በቂ የቴክኒክ፣ የኃብትና የዕውቀት ድጋፍ መገኘት**
- **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ 3፡ የላቀ የማኅበረሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ**
  **ስትራቴጂያዊ ውጤት 3፡ የህዝብ ባለቤትነት፣ አመኔታና ቅቡልነት**

## 3.2 የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂያዊ ውጤቶች መግለጫ

የሚከተለው ሠንጠረዥ የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችንና ውጤቶች መግለጫን የሚያቀርብ ሲሆን ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኩ ከርዕዩና ከስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ትስስር ያመለክታል ። በዚህም ስትራቴጂዎች የኮሚሽኑን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት የሚኖራቸውም ሚና መመርመር ይቻላል ።

**ሠንጠረዥ 4፡ የስትራቴጂ፣ ርዕይና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ትስስር**

| ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ / አምድ | ስትራቴጂያዊ ውጤት | ከርዕዩ ጋር ያላቸው ትስስር | ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ለመፍታት ስለማስቻላቸው |
|---|---|---|---|
| **የላቀ ሀገራዊ ምክክር፣** | **የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት** | በሕዝብ ምክክርና መግባባት ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያ ተፈጥራ ማየት፤<br>**<u>ትስስር</u>**<br>የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ በመድረስ የርዕዩን ውጤቶች ከማስፈጸም አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ | የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት በመሠረታዊ አጀንዳዎች ላይ በአጠረ ጊዜ በጥራት ከስምምነት ላይ ለመድረስ ያስችላል። ከዚህም በተጨማሪ ተዓማኒነት ያለው የኃብት አጠቃቀምን ዕውን ያደርጋል። ከዚህም በተጨማሪ ስትራቴጂያዊ ውጤቱ ከበጀት፣ ከልምድ እና ከአቅም ግንባታ ጋር የተያያዙ ስትራቴጂያዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ያስችላል። |
| **ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ትስስር** | **በቂ የቴክኒክ፣ የኃብትና የዕውቀት ድጋፍ መገኘት** | **<u>ትስስር</u>**<br>ሕዝባዊ ምክክሮችን ለማሳካት የሚያስችል ቴክኒካዊ ቁሳዊና የዕውቀትና የኢንፎርሜሽን ግብዓትን ለማሟላትና ተቋማዊ ብቃትን ለመፍጠር ያስችላል። | ከብቃት ጋር የተያያዙ አብዛሃኛዎቹን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ የኮሚሽኑን ቅቡልነት የሚያጎለብት ውጤት ነው። |
| **የላቀ የህዝብ ተሳትፎና ባለቤትነት** | **የህዝብ አመኔታና ቅቡልነት** | **<u>ትስስር</u>**<br>ስለምክክር ሂደቱ መረጃን ተደራሽ በማድረግ መግባባትንና ሰላምን ለማምጣት ያስችላል። | አካታችና ወካይ ምክክር ለማድረግ ስለሚያስችል የህዝብ ተሳትፎን በማረጋገጥ ህዝቡ የሂደቱ ዋነኛ ባለቤት እንዲሆን ያስችላል። |

# ክፍል አራት ፡ ስትራቴጂያዊ ግቦች መለኪያዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች

ስትራቴጂያዊ ግቦች ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን ወይም ስትራቴጂያዊ ውጤቶችን ለማሳካት ሲባል የሚዘጋጁ ሲሆን ባህሪያቸውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን ወይም ስትራቴጂያዊ ውጤቶችን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ናቸው፤
- ቀጣይነት ያለው መሻሻልን የሚያሳዩ ናቸው፤
- ስትራቴጂው ወደ ኦፕሬሽን የሚቀየርበት ነጥብ ነው፤
- መለኪያዎች የሚመሠረቱበት ነው፤
- ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች የሚመነጩበት ነው፤

ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች በስትራቴጂያዊ ግቦች ላይ የሚመሠረቱ ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚመለከቱ መለኪያዎች በባህሪያቸው ስትራቴጂያዊ ናቸው፡፡ በዚህ ሪፖርት የቀረቡ ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች ተቋማዊ ውጤትን ብቻ የሚለኩ ሲሆን በዓላማ ስኬትና በተሰጡ አገልግሎቶች ውጤት ላይ ብቻ ይመሠረታሉ፡፡

ስትራቴጂያዊ ዒላማዎች ከዕቅዱ አንጻር ከመቶኛ የተቀመጡ ሲሆን የአፈጻጸም ደረጃ የተወሰደው ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር የክትትልና ግምገማ አሠራር መመሪያ ነው፡፡ ይህም የኮሚሽኑን አፈጻጸም ከአገሪቱ የአፈጻጸም ደረጃ ጋር ለማስተሳሰር ያስችላል፡፡

የሚከተለው ሠንጠረዥ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን እና ስትራቴጂያዊ ግቦችን፣ ስትራቴጂያዊ መለኪያዎችንና የአፈጻጸም አመልካቾችን ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡ ስትራቴጂዊ የትኩረት መስኮች፣ውጤቶችና ግቦች**

| ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዊ ውጤት | ግቦች (11) |
|---|---|---|
| የላቀ  ሀገራዊ ምክክር ሂደት | የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት | ▪ የምክክር ተሳታፊዎችን እርካታን ማሳደግ<br>▪ የበጀት ውጤታማነትን ማሳደግ<br>▪ የምክክር ሂደት ጥራትን ማሳደግ<br>▪ የኢኮቴ አጠቃቀምን ማሳደግ<br>▪ ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ<br>▪ የምክክር ተሳታፊዎችን ብቃት ማሳደግ |
| ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ትስስር | **በቂ የቴክኒክ የኃብትና የዕውቀት ድጋፍ መገኘት** | ▪ የፋይናንስና ቴክኒክ አቅርቦትን ማሳደግ<br>▪ የስትራቴጂያዊ አጋሮች ቁጥርና ዓይነትን ማሳደግ |
| የላቀ የህዝብ  ተሳትፎ፤ | የጎለበተ የህዝብ  ባለቤትነት፣ አመኔታና ቅቡልነት | ▪ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣<br>▪ የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ፣<br>▪ የምክክር አካታችነትንና ውክልናን ማሳደግ፣ |

## ሠንጠረዥ 6፡ ስትራቴጂዊ ስኮር ካርድ - ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች፣ ዒላማዎች፣ የአፈጻጸም ደረጃዎችና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች

**የትኩረት መስክ 1፡ የላቀ ሀገራዊ ምክክር**

**ስትራቴጂያዊ ውጤት 1፡ የምክክር ሂደት ቅልጥፍናና ውጤታማነት**

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ተከታይና ቀዳሚ ስትራቴጂያዊ መለኪያ | መነሻ አፈጻጸም | ዒላማ (%) | የአፈጻጸም ደረጃ | | | ስትራቴጂያዊ እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዝ | መ | ከ | |
| የምክክር ተሳታፊዎች እርካታን ማሳደግ | ያደገ የምክክር ተሳታፊዎች እርካታ በመቶኛ (ቀዳሚ መለኪያ) | - | 100 | < 60 | 79 ≥ 60 | ≥ 80 | ▪ የተሳታፊዎች ቅሬታና አቤቱታ አፈታት ሥርዓት ፕሮጀክት<br>▪ የተሳታፊዎች እርካታ ሰርቬይ ፕሮጀክት<br>▪ የተሳታፊዎች ወቅታዊ ግብረ መልስ ሥርዓት ፕሮጀክት |
| | የቀነሰ የምክክር ተሳታፊዎች ቅሬታ በመቶኛ (ተከታይ መለኪያ) | - | 5 | < 60<br>(3) | 79 ≥ 60<br>(4) | ≥ 80<br>(≤ 5) | |
| የበጀት ውጤታማነትን ማሳደግ | ለታለመለት ዓላማ የዋለ የበጀት መጠን ዕድገት በመቶኛ (ቀዳሚ መለኪያ) | - | 100 | < 60 | 79 ≥ 60 | ≥ 80 | |
| የምክክር ሂደት ጥራትን ማሳደግ | ለምክክር ከቀረቡት አጀንዳዎች ስምምነትና መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች ብዛት በመቶኛ፣ (ተከታይ መለኪያ) | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | ▪ የተቀናጀ የምክክር አሠራር (የአጀንዳ አቀራረጽና ቅደም ተከተል አወጣጥ፣የአወያዮችና ሰብሳቢዎች ምልመላና መረጣ፣ የምክረ ሃሳቦች አፈጻጸም ክትትል ሥርዓት ፕሮጀክት፣ ዓመታዊ የምክክር መድረኮች የጊዜ ሰሌዳ ወዘተ) ቀረጻ ፕሮጀክት፤ |
| | በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ነጥረው የወጡ ምክረ ሃሳቦች ብዛት፣<br>(ቀዳሚ መለኪያ) | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢኮቴ አጠቃቀምን ማሳደግ | በኢኮቴ አማካይነት የተካሄዱ የምክክር ውይይቶች ብዛት በመቶኛ፣ (ተከታይ) | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | ▪ **የኢኮቴ ልማት ፕሮግራም**<br>○ የድረ ገጽ ልማት ፕሮጀክት<br>○ የሶፍትዌርና አፕሊኬሽን ልማት ፕሮጀክት<br>○ የመረጃ ቋት ግንባታ ፕሮጀክት<br>○ የኢኮቴ ሥልጠና ፕሮጀክት |
| | በዕቅድ ከተያዙ ሶፍትዌሮችና አፕሊኬሽኖች ሥራ ላይ የዋሉ ሶፍትዌሮች ብዛት በመቶኛ (ቀዳሚ) | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| | በመረጃ ቋት የተያዙ የሂደቱ መረጃዎች ብዛት በመቶኛ፣(ቀዳሚ) | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| የሠራተኞች/ ሥራ መሪዎች/ተባባሪዎች ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ ሠራተኞች ብዛት በመቶኛ፣ | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | **የሥልጠናና የሰው ኃብት ልማት ፕሮግራም**<br>○ የሥራ መሪዎች ሥልጠና ፕሮጀክት<br>○ የሠራተኞች ሥልጠና ፕሮጀክት<br>○ የተባባሪዎች ሥልጠና ፕሮጀክት |
| | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ ሥራ መሪዎች ብዛት በመቶኛ፣ | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ ተባባሪዎች ብዛት በመቶኛ፣ | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| የምክክር ተሳታፊዎችን ብቃት ማሳደግ | ስልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋኘጠ የምክክር ተሳታፊዎች ብዛት በመቶኛ | - | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | ▪ የምክክር ተሳታፊዎች ሥልጠና ፕሮጀክት |

## የትኩረት መስክ 2፡ ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ትስስር ና ብቃት፤
## ስትራቴጂያዊ ውጤት 2፡ የቴክኒክ፣ የኃብትና የዕውቀት ድጋፍ

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂያዊ መለኪያ | መነሻ አፈጻጸም | ዒላማ | | | የአፈጻጸም ደረጃ | | | ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2015 | 2016 | 2017 | ዝ | መ | ከ | |
| የፋይናንስና ቴክኒክ አቅርቦትን ማሳደግ | ያደገ የፋይናንስ አቅርቦት በመቶኛ | - | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | **የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ ማፈላለግ ፕሮጀክት** |
| | የተከናወኑ የልምድ ልውውጦች ብዛት | - | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | |
| | በድጋፍ የተገኘ የዓለም አቀፍ የምክክር ባለሙያ ብዛት | - | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | |
| የስትራቴጂያዊ አጋሮች ዓይነትና ቁጥርን ማሳደግ | የተፈረሙና ተግባራዊ የሆኑ የጋራ ስምምነቶች ብዛት፣ | - | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | ▪ **የቤንችማርኪንግና የዕውቀት ሥራ አመራር ፕሮጀክት** |
| | ከኮሚሽኑ ጋር አጋርነት የፈጠሩ ተቋማት/ አካላት ዓይነትና ብዛት | - | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተቀረጹና ተግባራዊ የሆኑ የአጋርነትና ትስስር ስትራቴጂና አሠራሮች ብዛት | | | | 100 | < 60 | 79 > 60 | ≥ 85 | **የስትራቴጂያዊ አጋርነትና ትስስር ስትራቴጂና አሠራር ቀረጻ ፕሮጀክት** |

| **የትኩረት መስክ 3፡ የላቀ የህዝብ ተሳትፎና ባለቤትነት፤<br>ስትራቴጂያዊ ውጤት 3፡ የጎለበተ የህዝብ ባለቤትነት፣ አመኔታና ቅቡልነት** | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ስትራቴጂያዊ ግቦች** | **ስትራቴጂያዊ መለኪያ** | **መነሻ አፈጻጸም** | **ዒላማ** | | | **የአፈጻጸም ደረጃ** | | | **ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች** |
| | | | **2015** | **2016** | **2017** | **ዝ** | **መ** | **ከ** | |
| የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ | ተግባራዊ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ብዛት | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | ▪ የኢንፎርሜሽ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ፕሮጀክት |
| | በግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች የተሳተፉ ሰዎች ብዛት | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ | የተከናወኑ የምክክር መድረኮች ብዛት፣ | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | ▪ ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቶች ድጋፍ ፕሮጀክት፣ |
| | በምክክር ሂደቱ የተሳተፉ አደረጃጀቶች ዓይነትና ብዛት | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የውይይት ማዕከላትና የተሳታፊዎች ጥምርታ | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| የምክክር አካታችነትና ውክልናን ማሳደግ፣ | በምክክሩ የተሳተፉ የህብረተሰብ ዓይነት ብዛት *በጥናት ከተለዩ የተሳታፊዎች ምድብ (ሴግመንት) አንጻር | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| | በምክክሩ የተሳተፉ ወጣቶች ብዛት *ከተሳታፊዎች ብዛት የወጣቱ ድርሻ ከጠቅላላ የወጣቶች ብዛት አንጻር በመቶኛ | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| | በምክክሩ የተሳተፉ ሴቶች ብዛት *ከተሳታፊዎች ብዛት የሴቶች ድርሻ ከጠቅላላ የሴቶች ብዛት አንጻር በመቶኛ | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |
| | በምክክሩ የተሳተፉ አካል ጉዳተኞች ብዛት በመቶኛ *ከተሳታፊዎች ብዛት የአካል ጉዳተኞች ድርሻ ከጠቅላላ የአካል ጉዳተኞች ብዛት አንጻር በመቶኛ | | | | | < 60 | 79 > 60 | ≥ 80 | |

# ክፍል አምስት፡ የትግበራ ስልቶች፤

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ስልቶች መከተል ያስፈልጋል ፡፡

- ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን በኮሚሽነሮች ም/ቤት ማፀደቅ፤
- ስትራቴጂውን ለማስፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር፤
- ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ለሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላትና ሠራተኞች ማጋራት፤
- ለስትራቴጂያዊ ፕሮግራሞች ተገቢውን ሀብት መድቦ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ፤
- የአፈፃጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድን ሳያሰልሱ ተግባራዊ ማድረግ፤

ዝርዝሩ የሚመለከተውን ይመስላል ፡፡

## 5.1 ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን በኮሚሽነሮች ም/ቤት ማጸደቅ

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ከሃሳብ ጀምሮ እስከ ረቂቅ ድረስ በኮሚሽነሮች ከፍተኛ የፖሊሲና ሙያዊ ድጋፍ ሲደረግበት የቆየ በመሆኑ ስትራቴጂውን በም/ቤቱ ማጸደቅ የመጀመሪያው ወሳኝ እና የሥነ ሥርዓት ጉዳይ ያደርገዋል፡፡ እና ለሌሎች ቀላልና የሥነ ሥርዓት ጉዳይ ነው ፡፡ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ሲጸድቅ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆንም በዕቅዱ የተዘጋጀውን የትግበራ ስልቶች በመመርመር ይሆናል ፡፡

## 5.2 ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር

ርዕዩንና ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስችል ብቃትን ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለመጠቀም የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ የሚፈጠረው አደረጃጀት በጥቂቱ የሚከተሉትን የሚያሟላ ሊሆን ይገባዋል፡፡

5.2.1 በኮሚሽኑ እሴት ፈጠራና ባህሪ ላይ የተመሠረተ፣

5.2.2 የኮሚሽኑን ርዕይና ስትራቴጂ ለማስፈጸም የሚያስችል ብቃት ላይ የተመሠረተ የሥራ ሂደትና የሥራ መደብ ዲዛይን፣

5.2.3 ቀልጣፋ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል፣

5.2.4 ሥራዎችን በአነስተኛ ጊዜ እና ወጪ በአነሰ ጥረትና ለማቀናጀትና ለማስተባበር የሚያስችል፣

5.2.5 የስትራቴጂ ቢሮን ስትራቴጂውን ለማስፈጸም በሚያስችል አግባብ ማደራጀት፣ ይህ ክፍል ሲደራጅ ስትራቴጂያዊ ሥርዓት

ለመዘርጋት፣ ለማስፈጸምና አፈጻጸሙን ለመተንተን የሚያስችል ብቃትን ይዞ ሊሆን ይገባዋል።

5.2.6 የሠራተኞችን ተነሳሽነት የሚያሳድግ መሆኑ፣ የሥራ መደቦች ዲዛይን ግልጽ ተግባራትንና አቅምን አሟጦ ለመጠቀም

የሚያስችል ጥረት የሚጠይቁ ሊሆኑ ይገባል። የሥራ መደቦች የሥራ ዝርዝር ፈጠራን፣ ተለዋዋጭ ፍሌክሲቢሊቲንና ቴክኖሎጂዎች መጠቀምን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባዋል።

## 5.3 ርዕዩንና ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ለሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላትና ሠራተኞች ማጋራት

የኮሚሽኑ ርዕይና ስትራቴጂ ለቁልፍ ባለድርሻ አካላት ሳያሰልሱ ማጋራት ለስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ተግባራዊነት ወሳኝ ጉዳይ ነው። የኮሚሽኑ ርዕይና ስትራቴጂ በሚከተሉት ስልቶች ሊጋሩ ይችላሉ።

5.3.1 ርዕዩንና ስትራቴጂውን ቀጣይነት ባለው የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂና ዕቅድ ማጋራት፤ በማንኛውም የአፈጻጸም ሂደት ምክክርንና መግባባትን መሠረት ማድረግ ይገባል። ዕቅድን በዕውቀትና በዕምነት መምራት ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ዕቅድን

ዕውቀትና ዕምነት አድርጎ ለመፈጸም የሚያስችል የተግባቦት ሥራ በመፈጸም ሂደት መተግበር ይገባል። የአመራሩ ሚና ርዕዩንና ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ማጋራት ነው። በርዕዩና ስትራቴጂው ላይ የጋራ አረዳድ መያዝና ማንኛውም ባለድርሻ አካል ዕቅዱን በመፈጸም ረገድ የሚኖረውን ሚና በግልጽ ማሳየት አስፈላጊ ነው።

5.3.2 በየደረጃው ለስትራቴጂው አስተዋፅኦ ያለው ስኮርካርድ መዘርጋት፡- ስትራቴጂያዊ ግቦችን ሊመግቡ የሚችሉ ግልጽና

ሊለኩ የሚችሉ ስኮርካርዶችን እስከ ሠራተኛው ድረስ ማዘጋጀት ለርዕዩና ለስትራቴጂው መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ

ይኖረዋል። ለዚህ ደግሞ የካስኬዲንግ ፕሮግራም መቅረጽና በአግባቡ መተግበር ይኖርበታል።

5.3.3 የዕውቅናና ሽልማት ሥርዓት መዘርጋት፡- ኮሚሽኑ በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የዕውቅናና ሽልማት ሥርዓት መዘርጋት

ይኖርበታል። የተለያዩ መድረኮችንም በማዘጋጀት በአስተዋጽኦ ላይ የተመሠረተ የዕውቅናና ሽልማት ፕሮግራም ሊኖር

ይገባል። ዕውቅናና ሽልማት መሰጠት የሚኖርበት በአፈጻጸም ላይ በመመስረት ሲሆን በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ ዕውቅናና

ሽልማት ለመስጠት በውጤት ላይ የተመሠረተ የአፈጻጸም ምዘናና ሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋት የኮሚሽኑ አንገብጋቢ

አጀንዳ ሊሆን ይገባዋል።

## 5.4 በጀትን ስትራቴጂያዊ ፋይዳ ባላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ ማዋል

በስትራቴጂ ደረጃ በጀት በሁለት ሊከፈል ይችላል። አንደኛው ስትራቴጂያዊ በጀት ሲሆን ይህም በጀት ለስትራቴጂያዊ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም የሚውል ይሆናል። በመሆኑም ለስትራቴጂያዊ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚሆን በጀት በዕቅዱ መሠረት መመደብና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን ለመተግበር የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር ይገባል።

## 5.5 የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ ስትራቴጂና ዕቅድ

ከኮሚሽኑ ባህሪና አጭር ዕድሜ አንጻር የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ግምገማ በየሩብ ዓመቱ ሊከናወን የሚገባው ሲሆን የኦፐሬሽን ግምገማ ደግሞ በየወሩ መከናወን ይኖርበታል። በዚህም መሠረት፣

### 5.5.1 የአፈጻጸም ክትትል

የአፈጻጸም ክትትል ከዕቅድ አንጻር አፈጻጸም የሚገኝበትን ደረጃ ለማየት የሚያስችል በተለይ በአመራሩና ሠራተኛው ብቻ የሚከናወን ተግባር ነው። በመሆኑም፣

(ሀ) በኮሚሽነሮች ም/ቤት ደረጃ በአፈጻጸም ክትትል ሪፖርት ላይ በየአሥራ አምስት ቀኑ ውይይት ሊደረግ ይችላል፣

(ለ) በመምሪያ የሥራ ክፍሎች ደረጃ በየሣምንቱ በአፈጻጸም ክትትል ሪፖርቶች ላይ ውይይት ሊደረግ ይችላል፣

(ሐ) በቡድን ደረጃ በየሳምንቱ በአፈጻጸም ክትትል ሪፖርት ላይ ውይይት ሊደረግ ይችላል፣

(መ) በግለሰብ ፈጻሚ ደረጃ የአፈጻጸም ክትትል በየዕለቱ ሊደረግ ይችላል።

የአፈጻጸም ክትትል ሪፖርት ከሦስት ገጽ የማይበልጥ ሪፖርት የሚቀርብበትና የሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርትም በዕቅድና አፈጻጸም መካከል ያለውን ልዩነትና ልዩነቱ በማነስ ከሆነ የአፈጻጸም ክፍተቱን ለመሙላት ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች የሚያሳይ መሆን ይገባዋል።

የአፈጻጸም ክትትል የአፈጻጸም ግምገማ መሠረት ሲሆን የሚዘጋጀውም የአፈጻጸም ሪፖርት በሚከተለው ቴምፕሌት መሠረት ይሆናል፤

| ተ/ቁ | የወሩ ዕቅድ | የወሩ ዕቅድ አፈጻጸም | የአፈጻጸም ልዩነት | የአፈጻጸም ማሻሻያ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |

### 5.5.2 ግምገማ

ስትራቴጂያዊ ግምገማ በተከታታይ ጊዜ በተሰባሰቡ የክትትል መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሳተፉበት፣ ጠለቅ ያለ ውይይት የሚካሄድበት እና የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድበት ነው። ግምገማ በሚከተለው ደረጃ የሚከናወን ይሆናል።

(ሀ) የአፈጻጸም ግምገማ ከቡድን እስከ ኮሚሽነሮች ም/ቤት ድረስ በየደረጃ የሚከናወን ይሆናል፣

(ለ) የኮሚሽኑ የአፈጻጸም ግምገማ በወር፣ በሦስት ወር፣ በመንፈቅና በየዓመቱ የሚከናወን ይሆናል፣

(ሐ) የአፈጻጸም ሪፖርት ከሠራተኞች ጀምሮ ሲገመገም በመጣ መረጃ ላይ የሚመሠረት ይሆናል፣

(መ) ኮሚሽኑ በየሩብ ዓመቱ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር አፈጻጸሙን መገገምገም ይኖርበታል፣

የሚከተለው ሠንጠረዥ የኮሚሽኑን የአፈጻጸም ግምገማ ስትራቴጂና ዕቅድ የሚያመለክት ነው።

| ግብ | ስትራቴጂያዊ እርምጃ | ውጤት (output) | የአፈጻጸም መለኪያ | መነሻ | ዒላማ | የመረጃ ምንጭ | ድግግሞሽ | ለመለካት ኃላፊነት ያለበት አካል | የሪፖርት አቀራረብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

# አባሪዎች

## አባሪ 1፡ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

### 1. የትንታኔው ዓላማ

በዚህ ክፍል የሀገራዊ ምክክር ምንነት፣ የምክክር ምዕራፎችና የሃገራት ተሞክሮ ይቀርባል፡፡ ጽሁፉ በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት የጋራ ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤ ለመያዝና ቁልፍ የስኬት ምክንያቶችን ለመለየት ያገለግላል፡፡ በሌላ በኩል ጽሁፉ የሀገራዊ ምክክር ምዕራፎችንና በየምዕራፉ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ስለሚያሳይ ለኮሚሽኑ እሴት ፈጠራ ትንታኔ መሠረት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጽሁፉ ሀገራዊ ምክክርን በመተግበር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ሪስኮችን አስቀድሞ ለመለየት ይጠቅማል፡፡

### 2. የሀገራዊ ምክክር ምንነት

ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በርካታ አገራት ዘላቂ ሰላምና ሁሉን አቀፍ የፖለቲካ መረጋጋት ለመፍጠር ብሔራዊ ምክክር (National Dialogue) እንዳደረጉ እና አንዳንዶቹ እያደረጉ እንደሚገኙ የጥናት ምንጮች ያመላክታሉ፡፡ ሰፊ መሠረት ያለው የፖለቲካ መረጋጋት ለመፍጠርና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ሁሉን አቀፍ፣ በብዝሃነት ላይ የተመሰረተ ሰፊ ፖለቲካዊ ውይይት ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ ግጭት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትና ዘላቂ ሰላም በታጣባቸው ሀገራት ልዩ ሁኔታውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ሀገራዊ ምክክር ማለት በአንድ ጥልቅ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ባለ ወይም ከጦርነት በኋላ ወይም ደግሞ ሥር ነቀል የፖለቲካ ለውጥ ለማድረግ ባሰበ ሀገር ውስጥ ለብሄራዊ አለመግባባት ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን አካታች እና አሳታፊ በሆነ መልኩ የሚለይበት፣ በጉዳዮቹም ላይ መግባባትና ስምምነት የሚፈጠርበት፣ ውይይት የሚካሄድበት፣ ከውይይቶቹም ምክረ ሃሳቦች የሚወጡበትና ምክረ ሃሳቦቹም ሲተገበሩ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት የሚመጣበት፣ ሥር የሰደዱ ችግሮች የሚፈቱበትና ሀገረ መሠረቱ በጠንካራ መደላድል ላይ የሚገነባበት ፖለቲካዊ ሂደት ነው (Huma Haiden (2019) National Dialogue, Lessons Learned and Success Factors in Helpdesk Report, P 2)፡፡

ሀገራዊ ምክክርን ሀገራዊ የሚያሰኘው ሰፊ ማኅበራዊ ውይይት የሚደረግበትና ሁሉን አቀፍ የማኅበረሰብ አካላት በስፋት የሚያሳትፍ መሆኑና በዚህም አጠቃላይ ሀገራዊ መግባባትንና ስምምነትን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ነው፡፡

የሀገራዊ የምክክር ሂደት መሠረታዊ ዓላማ ቁልፍ ሀገራዊ አጀንጃዎችን በውይይት በመለየት፣ በሀገሩ ታሪክ ምክንያት የተፈጠሩ የተዛቡ ጉዳዮችን በመለወጥ አዲስ የለውጥ ማኅበራዊ ስምምነት (New Social Contract) የሚደረግበትም ሂደት ነው፡፡ የምክክር ሂደትን በተመለከተ በተካሄዱ ጥናቶች መሠረት የሀገራዊ ምክክር ተጠባቂ ዋና ዋና ውጤቶች (Huma Haiden (2019) p 2)፡

- ያደገ የውይይት፣ የምክክርና ችግሮችን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የመፍታት ባህል፤
- በችግሮች ዙሪያ እና በምንጮቹ ላይ ተወያይቶ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ፤
- ከተረሱበት የተመለሱና ተግባራዊ መሆን የጀመሩ ጠቃሚ ነባር እሴቶችና ልምዶች፤
- በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎአቸው የጨመረ የተገለሉ ማኅበረሰቦች፤
- የሰፋና ሁሉንም የፖለቲካ ተዋናዮች ሊያሳትፍ የሚችል የፖለቲካ ምሕዳር፤

ግጭቶች ሁሌም የሚኖሩና ተፈጥሮአዊ ናቸው፡፡ ዋናው ጉዳይ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንደ ሀገር፣ እንደ ተቋምና እንደ ግለሰብ በሰላማዊና ሕጋዊ አግባብ መፍታት የሚያስችል አካሄድ መኖሩ ነው፡፡

## 3. **የሀገራዊ ምክክር ሂደት**

የሀገራዊ ምክክር በአራት ተከታታይ ምዕራፎች የሚከናወን ሰፊ መሠረት ያለው የሀገራዊ ለውጥ ሂደት አካል እንደ ሆነ በርካታ ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ በእኛ ሀገር ተሞክሮ ደግሞ አራት ምዕራፍ ያሉት ሂደት ሲሆን እነዚህ ምዕራፎች የቅድመ ዝግጅት፣ የዝግጅት፣ የምክክር ሂደትና የትግበራ ምዕራፎች ናቸው፡፡

### 3.1 የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ

የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ቀጣይ ሥራዎችን ለመፈፀም የሚረዱ የማመቻቸት፣ የሕጋዊ ማዕቀፍን የመዘርጋት፣ የሥልጣንና ኃላፊነት ውሳኔ (Mandate)፣ የኮሚሽኑን ተቋማዊ አደረጃጀት ማዋቀር፣ ለምክክር ሥራዎች የአሠራርና የአፈፃጸም መመሪያዎችን ማዘጋጀትን፣ በቂና የተሟላ የሰው ኃይል ማደራጀትንና ወደ ሥራ ለማሰማራት ማብቃትን የሚመለከት ነው፡፡

### 3.2 የዝግጅት ምዕራፍ፤

የመወያያ አጀንዳዎች፣ አወያዮችና ተወያዮች የሚመረጡበት፣ መስፈርቶች የሚለዩበት፣ ተቀርፀውና ተወስነው የሚደራጁበት ነው። ሀገራዊ ቁልፍ አጀንዳዎች የሚቀረፁበት ደግሞ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ቁልፍ ሀገራዊ ጉዳዮችን ለመለየት የሚያስችሉ አነስተኛ ሕዝባዊ ውይይቶችና ስብሰባዎችን በማድረግና ወሳኝ ጉዳዮች ለቀጣይ ውይይትና ምክክር ዝግጁ የሚሆኑበት ደረጃ ነው። በመሆኑም ይህ ምዕራፍ ለቀጣዩ ወሳኝና ሰፊ ለሆነው የምክክር ሂደት መሠረት የሚጣልበት ነው።

### 3.3 የሂደት ምዕራፍ

አስፈላጊ የሆኑ የተቋማዊ ጉዳዮች መስመር ከያዙና ለሀገራዊ ምክክር የሚሆኑ ጉዳዮች ከተለዩ ቀጣዩና ዋናው ምዕራፍ ሕዝቡን በየደረጃው በማወያየት፣ በምክክር እንዲሳተፍ በማድረግ ወሳኝ የሆኑ ስምምነቶችና መግባባቶች የተፈጠረባቸውን ሀገራዊ የመፍትሄ አቅጣጫዎችና ነጥቦችን አንጥሮ ማውጣትና ምክረ ሀሳቦችን ማመንጨት እና ነጥቦችን አንጥሮ ማውጣት ና ምክረ ሀሳቦችን ማመንጨት ነው።

### 3.4 የትግበራ ምዕራፍ

በዚህ ደረጃ በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ነጥረው የወጡና ስምምነትና መግባባት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች ወደ ተግባር የሚለወጥበት ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ በርካታ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉ ሲሆን በተጨባጭ ተግባራዊ የማድረግ፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች የሚከናወኑበት እንዲሁም በቀጣይነትና በዘላቂነት የምክክር ሂደቱ ስኬታማነት የሚረጋገጥበት ደረጃ ነው።

የሀገራዊ ምክክር ስኬታማነቱ የሚረጋገጠው ከዚህ በላይ በተቀመጡት ሦስት ምዕራፎች ስኬታማ አፈፃጸም ሲሆን በተለይ በምዕራፍ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱት ተግባራት የበለጠ ወሳኝ መሆናቸውን የሌሎች አገሮች ልምዶች ያመለክታሉ። ምክንያቱም አንድ ሀገራዊ ምክክር ስኬታማነቱ የሚረጋገጠው አንደኛ በቁልፍ ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ሰፊ መሠረት ያለው መግባባትና ስምምነት ላይ ሲደረስ፣ እንዲሁም ሁለተኛ እነዚህን ጉዳዮች በአግባቡ በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው ። ለዚህ ደግሞ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል።

በሌላ በኩል ከፍተኛ የተቋማዊ አቅም ጉድለትና ዋልታ ረገጥ አመለካከት ባለባቸው ሀገራት የዝግጅት ምዕራፍም ቢሆን ኃብትና ጊዜ ፈጅ ሊሆን ስለሚችል ምክክርን በተፈለገው ደረጃ በአንገብጋቢ አጀንዳነት ማስቀጠል ፈታኝ ሊሆን ይችላል።

## 4. የሀገራዊ ምክክር ስኬት መሠረቶች

ሀገራዊ ምክክር ያደረጉ ሀገራት በሙሉ የተሳካ ለውጥ ያደርጋሉ የሚል ድምዳሜ እንደሌለ ጥናቶች ያመላክታሉ። እንዲያውም በርካታ ሀገራዊ ምክክሮች እንዳልተሳኩ ጥናቶች ያመለክታሉ (Huma Haiden (2019), P 2)። ለምሳሌ ያህል፣ የየመን፣ የኢራቅ፣ ደቡብ ሱዳና ሱዳን ያልተሳኩ ከሚባሉት ውስጥ ናቸው። በሌላ በኩል ጥቂት ሀገሮች በሀገራዊ ምክክር ሂደት አልፈው የተሳካላቸው አሉ። ለአብነት ያህልም ፖላንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቱኒዚያ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። ጥናት አድራጊዎች የሚከተሉትን የሀገራዊ ምክክር ቁልፍ የስኬት ነጥቦች አስቀምጠዋል።

### 4.1 የፖለቲካ ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነት

ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ፣ ሂደቱን ከልብ ለመደገፍ፣ የተለዩና መግባባትና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና በልሂቃን ዘንድ ሙሉ ፈቃደኝነት፣ ስምምነት፣ እገዛና ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። የፖለቲካ ፈቃደኝነት የሚገለጽባቸው መንገዶችም ሀገራዊ ምክክር የተፈለገበት ዓላማ ሃቀኝነት፣ በምክክር ዝግጅትና ሂደቱ ላይ በሙሉ ልብ መሳተፍ፣ ሀገራዊ ባለቤትነትን ማረጋገጥ፣ ምክረ ሃሳቦችን የመፈጸም ዝግጁነት፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የፖለቲካ ተዋናዮች በሀገራዊ የምክክር ሂደቱ ላይ ከልብ በመነጨ ፍላጎት የማይሳተፉና ለይስሙላ ብቻ የሚሳተፉ ከሆነ አጠቃላይ የምክክር ሂደቱ የታለመለትን ውጤት ሊያመጣ አይችልም። ለዚህ እንደ ማሳያ ሊጠቀስ የሚችለው የደቡብ ሱዳን የምክክር ሂደት ነው። በደቡብ ሱዳን የምክክር ሂደት የተሳተፉ ዋና ዋና የፖለቲካ ተዋናዮች ወደ ሂደቱ የገቡት በእውነት ለምክክር ሂደቱ መሠረታዊ ዓላማ ተገዢ ሆነው ሳይሆን የየራሳቸውን የሥልጣን መንበር ለማደላደል ጊዜ ለመግዛት በማሰብ በመሆኑ የታቀደለትን ውጤት ሊያመጣ አልቻለም። በመሆኑም ያለ ተገቢና ከልብ የመነጨ ፖለቲካ ፈቃደኝነት የሚደረግ የምክክር ሂደት ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል አይደለም። የደቡብ ሱዳን የምክክር ሂደት እስካሁን ድረስ ውጤታማ ሊሆን ያልቻለበት ሌላው ምክንያት ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች

በዋነኛነት በሂደቱ እምነት አድሮባቸው መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ሳይሆን የተሳተፉት በውጭ ኃይሎች ግፊት ስለነበር ነው፡፡

## 4.2 ሀገራዊ ምክክሩ ከሌሎች ሀገራዊ ሥርዓቶችና የለውጥ ሂደቶች ጋር መተሳሰር

ሀገራዊ ምክክሩ ከሌሎች ዘርፈ ብዙ የአገራዊ ለውጥ ሂደቶች ጋር ተጣጥሞ፣ ተመጋግቦና ተቀናጅቶ የሚፈፀም ሂደት መሆኑ መሠረታዊና ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ያስችላል፡፡ ሀገራዊ ምክክር ከሀገራዊ የለውጥ ሂደቶች ጋር መጣጣምና መናበብ የማይችል ከሆነ እርስ በርስ ለመደጋገፍና ሀገራዊ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የማያስችል ይሆናል፡፡ የሀገራዊ የምክክር ሂደቱ ከሌሎች የፖለቲካ ሂደቶች የተለየና የተነጠለ ከሆነ በውጤቱ ላይ አሉታዊና አፍራሽ ተፅዕኖዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ በሊቢያ ሲካሄድ የነበረው የምክክር ሂደት ከሌሎች የፖለቲካ ሂደቶችና ቁልፍ ተቋማዊ ሥርዓቶች ጋር ግልፅ የሆነ ግንኙነትና ትስስር አልነበረውም፡፡ በተለይ ደግሞ የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ከሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነትና ተፅዕኖ የሌለው በመሆኑ የሚጠበቀውን ያህል ውጤት ሊያመጣ አልቻለም፡፡

## 4.3 በቁልፍ ባለድርሻ አካላት ዘንድ በሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊነትና አሠራር ላይ የጋራ መግባባት መኖሩ

በሀገራዊ ምክክሩ የሚነሱ መሠረታዊ የመግባቢያ ነጥቦች፣ አጠቃላይና ዋና ዋና ሀገራዊ ዓላማዎችና አንኳር በሆኑ የሂደቱ ነጥቦች ላይ በአጠቃላይ ባለድርሻ አካላት በተለይ በዋና ዋና ተዋናዮች መካከል የጋራ መሠረት ሊኖር ይገባል፡፡ በዋና ዋና እና መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ዋልታ ረገጥ የሆነና መርህን የጣሰ አቋም በመያዝ በጥርጣሬና በመፈራራት መተያየት የምክክር ሂደቱን ሊያስተጓጉልና ሊያደናቀፍ ስለሚችል ዋልታ ረገጥ ዕይታዎችን ማቀራረብና የምክክር አውዱን ማስፋት ይጠይቃል፡፡ በተለይ በገዢውና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ወሳኝ በሆኑ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎችና በዓላማው ላይ የጋራ መሠረት ይዘው መነሳት ጠቀሜታ አለው፡፡ ለዚህ እንደ አብነት የሚጠቀሰው እ.ኤ.አ. ከ2005 እስከ 2011 በሱዳን እንዲሁም በየመን የተደረጉትን የምክክር ሂደቶች ማየት ይቻላል፡፡ በወቅቱ በተፋላሚ ኃይሎች መካከል በምክክር ሂደቱ ዓላማ ላይ የጋራ እይታና ግንዛቤ የሌለ በመሆኑና ተዋናዮቹ ሊያሳኳቸው የሚፈልጓቸው ጠባብና የየራሳቸው የተለያዩ አጀንዳዎችን ይዘው በመገኘታቸው በሁለቱም አገራት የነበረው የምክክር ሂደት ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ በተለይ በየመን የብሔራዊ የምክክር ኮንፈረንሱ (Yemeni National Dialogue Conference) በአካታችነቱና በቴክኒካዊ ብቃቱ የተመሰከረለት እና የወጡት ምክረ ሃሳቦች ውጤታማ ሊባሉ የሚችሉ

ቢሆኑም ተግባራዊ የሚሆኑበት ዕድል እጅግ የጠበበ ሆኖ ስለተገኘ የመን እስከዛሬም ድረስ ደም አፋሳሽ እልቂትና የሰብዓዊ ቀውስ ውስጥ ልትገኝ ችላለች። በተመሳሳይ በቬኔዙዌላ በገዢው ቻቪስታ (Chavistas) እና በተቃዋሚ ቡድኖች መካከል በኢኮኖሚ አጀንዳዎች ዙሪያ መግባባት ላይ የተደረሰ ቢሆንም በሌሎች የምክክር አጀንዳዎች በተለይም በዴሞክራሲ ጉዳዮች ላይ እጅግ የተራራቀና ተቃራኒ ጎራ ላይ ያለ ልዩነት (Diametrically Opposite) ይዘው እስከ ምክክሩ ማጠናቀቂያ ድረስ ስለዘለቁ በምክክር ሂደቱ ተቃራኒ ጎራ ላይ ያሉትን ለማቀራረብም ሆነ የሚገናኙባቸውን የጋራ ነጥቦችን ለመለየት አዳጋች ሁኔታ ፈጥሮ ነበር ።

### 4.4 በሕዝብ ቅቡልነት ማግኘቱ (Public Buy - in)፡

የሕዝብ ቀጥተኛ ድጋፍ መኖሩ ወይም አለመኖሩ በሂደቱ ውጤታማነትና ስኬት ላይ ዋንኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡ ፡ ሂደቱን ሕዝቡ እንዲገዛው ለማድረግ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በቂ መረጃ መስጠት፣ የሚዲያ ግንኙነትና ተሳትፎን ማጠናከር፣ በምክክር ሂደቱ ላይ የሚኖር ተሳትፎን ማሳደግ ወዘተ አስፈላጊ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የመፍትሄ እርምጃዎችን ትግበራ ላይ ህዝቡ ዋንኛ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ይገባል። የምክክር ሂደቱን ውጤታማነት ከሚያሳኩ መሠረታዊ ነጥቦች አንዱና ዋነኛው የምክክር ሂደቱንም ሆነ የተገኙ ምክረ ሀሳቦችን እንዲሁም የመፍትሄ እርምጃዎችንና አቅጣጫዎችን ለሁሉም የሕዝብ አካላት በቂና ወቅታዊ መረጃ መስጠት ነው። ይህም በተለይ ሕዝቡን የሚወክሉትን ተወካዮች በስፋት ለመምረጥና በዚህም ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው። ለዚህ እንደ አንድ አብነት ሊወሰድ የሚችለው የፖላንድ ብሔራዊ የምክክር ልምድ ነው። በፖላንድ የምክክር ሂደቱ ሲጀመር ጠንካራ የሚዲያና የሕዝብ ምክክር (Media and Public Consultation) ስትራቴጂ ተቀርፆ በአግባቡ ተግባራዊ በመደረጉ የምክክር ሂደቱን ያሳለጠ ከመሆኑም ባሻገር በፖለቲካ ምህዳሩ ሲታዩ የነበሩትን ክፍተቶች በመለየትና በመሙላት የሕዝብ አመኔታን አትርፏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኢራቅ የተደረገው የምክክር ሂደት ለሕዝቡ በበቂ መጠንና ስፋት የማሳወቅ ዘመቻ የተከናወነ ባለመሆኑና ሂደቱ በራሱ በቂ የሚዲያ ሽፋን ያልነበረው በመሆኑ የሚፈለገውን ያህል የመረጃ ልውውጥና ተሳትፎን በብቃት የመለሰ አልነበረም። በምክክር ሂደቱ የተቃዋሚና ተፎካካሪ ኃይሎችና የሲቪክ ማኅበራት በበቂ ሁኔታ ያልተወከሉ በመሆኑ የተሳትፎ ምህዳሩ ጠባብና በቅርበት ያሉ የአንድ ፖለቲካ ጎራ የምክክር ሂደት ብቻ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም የምክክር ሂደቱ የሚጠበቅበትን ውጤት ሳያስገኝ ቀርቷል። በሌላ በኩል በየመን የነበረው የምክክር ሂደት ምንም እንኳን የኮሚኒኬሽንና የሚዲያ ስትራቴጂ የተዘጋጀ ቢሆንም በተለይ በሂደቱ ላይና በአስፈላጊነቱ ላይ ለምክክር ሂደቱ ርቀው ለሚገኙ ዜጎች

ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ሥራዎች በአግባቡ ያልተከናወኑ በመሆናቸው የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኙ አልተቻለም።

## 4.5 የሌሎች ሀገራትንና ሀገር በቀል ልምዶችን መጠቀም

በሀገራዊ የምክክር ሂደቱ የሌሎችን አገራት የላቁና ተስማሚ ተሞክሮን ከቀደሙና አገር በቀል ከሆኑ ልምዶች ጋር በማጣጣምና በማዋሃድ ተግባራዊ ማድረግም ተገቢ ነው። ከሌሎች አገራት ልምድና ተሞክሮ መማርና ጠቀሜታ ያላቸውን ልምዶች በመውሰድ ከራስ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣምና አገር በቀል ልምዶችን መጠቀም በጥንቃቄ ሊከወን የሚገባው ጠቃሚ ግብዓት ነው።

የምክክር ሂደቱ በዝግጅት ደረጃ አላስፈላጊ ጊዜ መውሰዱና በዚህም ሂደቱ የዘገየ ከሆነ ሕዝቡ በሂደቱ ወደ ተስፋ መቁረጥ በመሄድ የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዳይወጣ ያደርገዋል ። ለዚህ እንደ አብነት ሊጠቀስ የሚችለው የየመን የብሔራዊ የምክክር ልምድ ነው። በየመን የምክክር ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ ወደ ሕዝቡ ወርዶ የውይይትና የምክክር ሥራ ሳይከናወን ለአንድ ዓመት ያህል ዘግይቶ ነበር። በዚህም የተነሳ በሕዝብ ዘንድ ሊኖር የሚገባውን ድጋፍና እገዛ ካለመገኘቱም በላይ በሂደቱ ዋነኛ ተዋናይ ለነበሩት የሂደቱን አፈፃፀምና ውጤት በሕዝቡ ዘንድ በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አልተቻለም።

የሌሎች ሀገራትን ልምድ ስንመለከት ከአራቱ የምክክር ደረጃዎች መካከል በተለይ በደረጃ 3 ማለት በስምምነትና መግባባት ሂደት ደረጃ እና በደረጃ 4 ማለትም በትግበራ ደረጃ ላይ መፈፀም የሚገባቸውን አለመፈፀም እንደሆነና በተለይ በዝግጅት ጊዜ እንደ ሁለቱ ደረጃዎቸ የጎላ ክፍተት እንደማያጋጥማቸው ያመላክታል። የኢትዮጵያን አፈፃፀም ስናይ ግን በአሁኑ ወቅት በቅድመ ዝግጅት እና ዝግጅት ጊዜ የሚፈፀሙት ተግባራት በአግባቡ መፈፀም ወይም አለመፈፀም ለሂደቱ መሳካት ቁልፍ ድርሻ ያለው መሆኑ ነው። ምክንያቱም የእኛ ሀገር የምክክር ሂደት አጀንዳዎችን ከመምረጥ ጀምሮ ምልዓተ ሕዝቡን በስፋት የሚያሳትፍ መሆኑ፣ የምክክር አጀንዳዎቹ እንደ አብዛኛዎቹ ሀገራት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይሆን ሰፊ ሀገራዊ አንድምታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ማትኮሩ፣ ሌሎች ሀገራት ያላቸው የቀደመ ልምድ የሌለ መሆኑ ሥራውን ውስብስብና ግዙፍ ያደርገዋል። በመሆኑም በቅድመ ዝግጅትና በዝግጅት ምዕራፍ መፈፀም የሚገባቸው ወሳኝ ጉዳዮችን በጥንቃቄና በአግባቡ ፈፅሞ ለቀጣዮቹ ምዕራፎች በቂ መነሻ መሆኑ የማያጠያይቅ ነው።

## 4.6 የውጭ ባለድርሻ አካላት ሚናና በአገራዊ ባለቤትነት መካከል ሚዛንን ማስጠበቅ

የምክክር ሂደቱ ከውጭ አካላት የፖለቲካ፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል። ይህ ድጋፍ ለሂደቱ ውጤታማነት የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ የሚኖረው ሲሆን ሆኖም ከድጋፉ ጋር ተያይዞ ሊመጡ የሚችሉ ተግዳሮቶች እንደሚኖሩ ይታመናል። ምክንያቱም የምክክር ሂደቱ ድጋፍና እገዛ ባደረጉ አካላት ተፅዕኖ ሥር ሊወድቅበት የሚችልበት ዕድልና አገጣሚም ሊኖር ይችላል። አጠቃላይ ሀገራዊ የምክክር ሂደቱ ደግሞ በመሠረታዊነት በሀገራዊ ባለቤትነት የሚከናወን ፖለቲካዊ ሂደት ነው። ስለዚህ የሀገራዊ ምክክር ቀጥተኛና ዋነኛ ተዋናዮቹ በአገር ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት ናቸው። ስለሆነም ሁለቱ አካላት ማለትም የውጭ ድጋፍና እገዛ አድራጊ አካላትና በሀገራዊ ባለቤቶች መካከል ትክክለኛና ሚዛኑን የጠበቀ አካሄድ መኖሩ ለሂደቱ ስኬታማነት አስተዋፅዖ አለው። ከውጭ የፋይናንስ ድጋፍ አንጻር በዕቅድ ይዘት ላይ ተጽዕኖ የሌለው ደጋፍ መቀበል አግባብነት ይኖረዋል። የቴክኒክ ድጋፍ ላይ ደግሞ የውጭ ባለሙያዎችን ከሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ጋር በማቀናጀት ማሠራት ነጻነትን ለመጠበቅና የዕውቀት ሽግግርን ለማረጋገጥ ይረዳል።

## 4.7 የአካታችነትና የተሳትፎ ደረጃ (The degree of inclusion and participation)፡-

በርካታ የንድፈ ሀሳብ ትንታኔዎች እንደሚያስቀምጡት ሀገራዊ ምክክር ውጤታማነት የሚረጋገጠውና ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በአንድ ሀገር ውስጥ ያለ ማኅበረሰብ በቀናነት (genuine) እና በስፋት ሲሳተፍ ነው። በዚህም የተዛቡ የኃይል ሚዛን ጉዳዮችን በመመለስ፣ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት መሆኑ በተጨባጨ ሲረጋገጥ፣ እንዲሁም በቁልፍ ጉዳዮች ውስጥ ሀሳቡንና አመለካከቱን ያለ ገደብ በነፃነት ሲገልፅ ነው። ሆኖም አካታችነትንና ተሳትፎን ለማረጋገጥ ሲባል ከመጠን በላይ የተለጠጠና ለአስተዳደር አመቺ ያልሆነና ውጤት አልባ ውይይቶችን ማድረግ ቁልፍ የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በአግባቡ በመለየት ለመመለስና ዘላቂ መፍትሄ የሚገኝባቸውን ቁም ነገሮች ለማግኘት የማይቻልባቸውን ሁኔታዎች እንዳፈጠሩ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ስለሆነም በአካታችናነት/ተሳትፎና በውጤታማነት መካከል ትክክለኛ ሚዛኑን የጠበቀ የምክክር ሂደት ሊኖር ይገባል። ይህን ሚዛን ለመጠበቅ ቁልፍ በሆኑና ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገባቸው ጉዳዮች ማትኮር፣ አንድ ዓይነት ፍላጎት ያላቸውን በመለየት ፍላጎቱን ሊወክሉ የሚችሉትን መርጦ በማሳተፍ፣ ዜጎች በሚመለከታቸው አጀንዳ ብቻ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክሎጂና አፕሊኬሽኖችን መጠቀም፣ ሚዲያ መጠቀም፣ ወዘተ ተጠቃሽ ዘዴዎች ናቸው።

## 4.8 የተወካዮች አመራረጥ ሂደትና የተወካዮች መምረጫ መስፈርት ትክክለኛነት (Representation and Selection Criteria) :-

በሀገራዊ ምክክር መድረክ ላይ ሊሳተፉ የሚገባቸውን የሕዝብ ተወካዮች ለመምረጥ የተሄደበት ሂደትና የመምረጫ መስፈርቶች ትክክለኛነት በአጠቃላይ የምክክር ሂደቱ ስኬታማነት ላይ ቁልፍ ድርሻ አለው። በመምረጫ መስፈርቱና ሂደቱ ላይ ሕዝቡ እምነት ከጣለበት በቀጣይ ለሚከናወኑ ተከታታይ ሥራዎች መሳለጥና መሳካት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል። በመሆኑም የምርጫ ሂደቱንና መስፈርቶችን በሕዝብ ዘንድ በግልፅ እንዲታወቅ፣ በቂ ግንዛቤ እንዲያዝበትና እንዲታመን ማድረግ ይገባል።

## 4.9 ውጤታማ ተቋማዊ ማዕቀፍና የድጋፍ አደረጃጀት (Institutional Framework and Support):-

የምክክር ሂደቱን ለመደገፍ የተደራጁ አካላት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በአግባቡ መወጣታቸው ለስኬቱ አስተዋጽዖ አለው። በመሆኑም ሴክሬታሪያቱን፣ አማካሪ ኮሚቴዎችን፣ ወዘተ ማደራጀትና በሌሎች ተቋማት ብቃት ነጻነትን ጠብቆ መጠቀም ተገቢ ነው።

## 4.10 በምክክር ሂደቱ ተለይተው የሚወጡ የመፍትሄ እርምጃዎች ተግባራዊነት (Provision of Implementation):-

በምክክር ሂደቱ ነጥረው በጋራ መግባባትና ስምምነት የተለዩ የመፍትሄ እርምጃዎች በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ በቂ የሀብት አቅርቦት፣ የክትትልና ምዘና፣ የተጠያቂነት፣ የአሠራርና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓትና ሂደት ሊኖር ይገባል። የመፍትሄ እርምጃዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ አካላት በቂ ተቋማዊ አደረጃጀት ያላቸው ወይም ደግሞ እንዳስፈላጊነት አዲስ አደረጃጀት ተዋቅሮ ተግባራዊ መደረግ ይገባዋል።

## አባሪ 2 ፡ የስትራቴጂያዊ መለኪያዎች መግለጫ -

| ግብ | መለኪያ | የመረጃ ምንጭ | ቀመር | መረጃው የሚሰበሰብበት ድግግሞሽ | መነሻ አፈጻጸም | ዒላማ | መለኪያው የሚገኝበት ቦታና ባለቤት | የመረጃው አግባብነትን የሚያረጋግጠው | የመረጃውን ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የምክክር ተሳታፊዎችን እርካታን ማሳደግ | ያደገ የምክክር ተሳታፊዎች እርካታ በመቶኛ | ሰርቬይ | መቶኛ | በየስድስት ወሩ | - | ≥80 | የኮሙኒኬሽን ሥራ ክፍል | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | የሥራ ክፍሉ ከፍተኛ ባለሙያ |
| የበጀት ውጤታማነትን ማሳደግ | ለታለመለት ዓላማ የዋለ የበጀት መጠን ዕድገት በመቶኛ | የውስጥ ኦዲት እና የፐርፎርማንስ ኦዲት ሪፖርቶች | የበጀትና የተሰጠ አገልግሎት መጠን ጥመርታ | በየዓመቱ | - | ≥80 | የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል | የኮሚሽነሮች ም/ቤት | የኦዲተሮች ቡድን |
| የምክክር ሂደት ጥራትን ማሳደግ | ስምምነትና መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች ብዛት በመቶኛ፣ | የኮሚሽኑ ም/ቤት | ለውይይት ከቀረቡ አጀንዳዎች ስምምነት የተደረሰባቸው መጠን በመቶኛ | በተመጡ አጀንዳዎች ላይ ውይይት ከሚጀመርበት ጊዜ አንስቶ በየስብሰባው ማጠቃለያ | - | ≥80 | የኮሚሽኑ ም/ቤት | ለጉዳዩ የተመረጡ ኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | አወያዮች |
| | በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ነጥረው የወጡ ምክረ ሃሳቦች ብዛት፣ | የኮሚሽኑ ም/ቤት | በውይይት ከተነሱ ዕጩ ምክረ ሃሳቦች ነጠረው ከወጡ መካከል ተቀባይነት | ሀገራዊ አጀንዳዎችን ለመለየት በተካሄዱ ስብሰባዎች እንደተጠናቀቁ | - | ≥80 | የኮሚሽኑ ም/ቤት | ም/ኮሚሽነር | አወያዮች |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ያገኙት በመቶኛ | | | | | | |
| የምክክር ሂደት ቅልጥፍናን ማሳደግ | በጸደቁ መመሪያዎች መሠረት የተከናወኑ ሀገራዊ የምክክር መድረኮች ብዛት | የኮሚሽኑ ም/ቤት | በጸደቁ መመሪያዎች መሠረት የተከናወኑሀሀ ገራዊ የምክክር መድረኮች ብዛት በመቶኛ | ሀገራዊ ምክሮች በተደረጉ በሳምንት ጊዜ ውስጥ | - | ≥80 | የኮሚሽኑ ም/ቤት | ም/ኮሚሽነር | አወያዮች |
| | ጸድቀው ወደ ተግባር የገቡ የአሠራር ሥርዓቶች (መመሪያዎች፣ መስፈርቶች፣ የአፈጻጸም ማኑዋሎች፣ ወዘተ) | የኮሚሽኑ ም/ቤት | ከጸደቁት መካከል ወደ ተግባር የገቡ የአሠራር ሥርዓቶች በመቶኛ | የአሠራር ሥርዓቶች በጸደቁ በሳምንት ውስጥ | - | ≥80 | ለጉዳዩ የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | ም/ኮሚሽነር | የኮሚሽነሮች ቡድን አባል |
| | በመረጃ ቋት የተያዙ የምክክር ሂደቱ መረጃዎች፣ | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | መያዝ ከሚገባቸው መረጃዎች መካከል ወደ መረጃ ቋት የገቡ መረጃዎች | በየወሩ | - | ≥80 | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | የኢኮቴ የመረጃ ቋት ባለሙያ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት በመቶኛ | | | | | | |
| በምክክር ሂደት የኢኮቴ አጠቃቀምን ማሳደግ | ሥራ ላይ የዋሉ ሶፍትዌሮች ብዛት በመቶኛ | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | መያዝ ከሚገባቸው መረጃዎች መካከል ወደ መረጃ ቋት የገቡ መረጃዎች በመቶኛ | በየሳምንቱ | - | >80 | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | የኢኮቴ የመረጃ ቋት ባለሙያ |
| | ሥራ ላይ የዋሉ አፕሊኬሽኖች ብዛት በመቶኛ፣ | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | ከተጠኑት አፕሊኬሽኖች መካከል ወደ ሥራ የገቡ ብዛት በመቶኛ | በሦስት ወሩ | - | >80 | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | የኢኮቴ የመረጃ ቋት ባለሙያ |
| | በኢኮቴ አማካይነት የተካሄዱ የምክክር ውይይቶች ብዛት በመቶኛ፣ | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | በኢኮቴ አማካይነት የተካሄዱ የምክክር ውይይቶች ከታቀደው አንጻር በመቶኛ፣ | በየሦስት ወሩ | - | >80 | የኢኮቴ የሥራ ክፍል | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | አወያዮች |
| የሠራተኞች/ ሥራ መሪዎች/ ተባባሪዎች | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ | የሰው ኃብት የሥራ ክፍል | ከሰለጠት መካከል የብቃት ፈተኛ | በየሦስት ወሩ | - | >80 | የሰው ኃብት ዳይሬክቶሬት | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | ዳይሬክተር |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | ሠራተኞች ብዛት በመቶኛ፣ | | ያለፉት በመቶኛ | | | | | | |
| | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ ሥራ መሪዎች ብዛት በመቶኛ፣ | የሰው ኃብት የሥራ ክፍል | ከሰለጠት መካከል የብቃት ፈተኛ ያለፉት በመቶኛ | በየሦስት ወሩ | - | ≥80 | የሰው ኃብት ዳይሬክቶሬት | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | ዳይሬክተር |
| | ሥልጠና ያገኙና ብቃታቸው የተረጋገጠ ተባባሪዎች ብዛት በመቶኛ፣ | የሰው ኃብት የሥራ ክፍል | ከሰለጠት መካከል የብቃት ፈተኛ ያለፉት በመቶኛ | በየሦስት ወሩ | - | ≥80 | የሰው ኃብት ዳይሬክቶሬት | የሥራ ክፍሉ ኃላፊ | ዳይሬክተር |
| የፋይናንስና ቴክኒክ አቅርቦትን ማሳደግ | ያደገ የፋይናንስ አቅርቦት በመቶኛ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽኑ ም/ቤት ሰብሳቢ | ከታቀደው የፋይናስ አቅርቦት የተገኘው በመቶኛ | በየሦስት ወሩ | - | ≥80 | የፋይናስ ዳይሬክቶሬት | የፋይናስ ዳይሬክተር | ዳይሬክተር |
| | የተከናወኑ የልምድ ልውውጦች ብዛት | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽኑ ምክር ቤት ሰብሳቢ | ከታቀደው አንጻር የተከናወኑ ቤንችማርኪን ግ ፕሮግራሞች ብዛት በመቶኛ | በየስድስት ወሩ | - | ≥80 | ለሥራው የተመደበው ኮሚሽነር | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽኑ ም/ቤት ሰብሳቢ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽኑ አባል |
| | በድጋፍ የተገኘ የዓለም አቀፍ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮ | ከታቀደው አንጻር የተገኙ የምክክር | በየሦስት ወር | - | ≥80 | ለሥራው የተመደበው | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች | ለሥራው የተመደበው |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምክክር ባለሙያ ብዛት | ች ቡድን ሰብሳቢ | ባለሙያዎች ብዛት በመቶኛ | | | | የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | ቡድን ሰብሳቢ ቢሮ | የኮሚሽነሮች ቡድን አባል |
| የስትራቴጂያዊ አጋርነት ውጤታማነትን ማሳደግ | የተፈረሙና ተግባራዊ የሆኑ የጋራ ስምምነቶች፣ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮ ች ቡድን ሰብሳቢ | ከታቀደው አንጻር ተግባራዊ የሆኑ ስምነቶች | በየሦስት ወር | - | >80 | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ ቢሮ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን አባል |
| | ከኮሚሽኑ ጋር አጋርነት የተፈጠሩ ተቋማት/ አካላት ብዛት | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮ ች ቡድን ሰብሳቢ | ከታቀደው አንጻር ተግባራዊ የሆኑ ስምምነቶች | በየሦስት ወር | - | >80 | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ ቢሮ | ለሥራው የተመደበው የኮሚሽነሮች ቡድን አባል |
| የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ | ተግባራዊ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ብዛት | የኮሙኒኬሽ ን የሥራ ክፍል | ከተዘጋጁት መካከል ተግባራዊ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ | በየሦስት ወሩ | - | >80 | የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | ዳይሬክተር | ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን ባለሙያ |
| | በግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች የተሳተፉ ሰዎች ብዛት በመቶኛ | የተወከለ የኮሚሽነሮ ች ቡድን መሪ | እንዲሳተፉ ከታቀደው የተሳተፉ ብዛት በመቶኛ | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |
| የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ፣ | የተከናወኑ የምክክር መድረኮች ብዛት፣ | የተወከለ የኮሚሽነሮ ች ቡድን መሪ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች ባዛት | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | | | | | | |
| | በምክክር ሂደቱ የተሳተፉ አደረጃጀቶች ዓይነትና ብዛት | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን መሪ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች ባዛት የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |
| | የውይይት ማዕከላትና የተሳታፊዎች ጥምርታ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን መሪ | ከታቀደው አንጻር የውይይት ማዕከላትና የተሳታፊዎች ጥምርታ | ውይይቶች በተጠናቀቁ በሳምንት ጊዜ ውስጥ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |
| የምክክር አካታችነትን ማሳደግ፣ | በምክክሩ የተሳተፉ የህብረተሰብ ዓይነት ብዛት *በጥናት ከተለዩ የተሳታፊዎች ምድብ (ሴግመንት) አንጻር | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን መሪ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች ብዛት የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |
| | በምክክሩ የተሳተፉ ወጣቶች ብዛት | የተወከለ የኮሚሽነሮ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | *ከተሳታፊዎች ብዛት የወጣቱ ድርሻ ከጠቅላላ የወጣቶች ብዛት አንጻር በመቶኛ | ች ቡድን መሪ | ባዛት የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | | | | | | |
| | በምክክሩ የተሳተፉ ሴቶች ብዛት *ከተሳታፊዎች ብዛት የሴቶች ድርሻ ከጠቅላላ የሴቶች ብዛት አንጻር በመቶኛ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን መሪ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች ባዛት የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |
| | በምክክሩ የተሳተፉ አካል ጉዳተኞች ብዛት በመቶኛ *ከተሳታፊዎች ብዛት የአካል ጉዳተኞች ድርሻ ከጠቅላላ የአካል ጉዳተኞች ብዛት አንጻር በመቶኛ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን መሪ | ከታቀደው የምክክር መድረኮች ባዛት የተከናወኑ መድረኮች በመቶኛ | በየወሩ | - | >80 | የተወከለ ኮሚሽነር ቢሮ | የተወከለ የኮሚሽነሮች ቡድን ሰብሳቢ | የቡድኑ አባል |

## አባሪ 3፡ የስትራቴጂያዊ እርምጃዎች መግለጫ (የፕሮጀክቶችና በጀት ትስስር)

| ተ/ቁ | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ | ባለድርሻ አካላት | በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ግቦች | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ወጪ በብር | ቁልፍ እሳቤዎችና ተግዳሮቶች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የተሳታፊዎች ቅሬታና አቤቱታ ሥርዓት ፕሮጀክት | ለሥራው የተወከለ ኮሚሽነር | ወደፊት የሚመደብ | • ዜጎች፣<br>• የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፤<br>• የምክክር ሂደቱ ተሳታፊዎች<br>• ሚዲያ<br>• መንግስት<br>• የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት | ▪ የተሳታፊዎች እርካታን ማሳደግ<br>▪ የተሳታፊዎች ቅሬታን መቀነስ | መስከረም 30፣ 2015 ዓ.ም<br><br>**በአንድ ወር የሚጠናቀቀ ፕሮጀክት** | 500,000 | ተሳታፊዎች ቅሬታና አቤቱታቸውን በግልጽነት ያቀርባሉ፤ | ለቅሬታዎች ፈጥኖ ምላሽ አለመስጠት፤<br><br>በቅሬታና አቤቱታ ሥርዓት ላይ ዜጎችና የምክክር ተሳታፊዎች በቂ ግንዛቤ አለማግኘት፤ |
| 2. | የተቀናጀ የምክክር አሠራር ቀረፃ ፕሮጀክት | የኮሚሽነሮች ሰብሳቢ | ወደፊት የሚመደብ | • ዜጎች፤<br>• የፖለቲካ ፓርቲዎች፣<br>• በምክክር ሂደቱ ተሳታፊዎች፤<br>• አወያዮች<br>• አመቻቾች | ▪ የምክክር ጥራትን ማሳደግ<br>▪ የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ | ህዳር 30፣2015 ዓ.ም<br>3 ወር ጊዜ የሚፈጅ ፕሮጀክት | 2,000,000 | • አሠራሮች ለመቅረጽ የሚችሉ ባለሙያዎች በገበያው ይገኛሉ፤<br>• የአሠራር ሥርዓቶቹ በበቂ ቁጥጥርና ተጠያቂነት ተግባራዊ ይሆናሉ፤ | ▪ የጥናቶች በወቅቱ አለመድረስ፤<br>▪ የአሠራር ሥርዓቶች ተመጋጋቢነት መጓደል፣ |

| ተ/ቁ | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ | ባለድርሻ አካላት | በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ግቦች | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ወጪ በብር | ቁልፍ እሳቤዎችና ተግዳሮቶች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3. | የኢኮቴ ልማት ፕሮግራም | የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ | የኢኮቴ ዳይሬክተር | | | በአጠቃላይ 6 ወር የሚፈጅ ፕሮግራም | **0** | | |
| 3.1 | የድረ ገፅ ግንባታ ፕሮጀክት | የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ | የኢኮቴ ዳይሬክተር | • ኮሚሽነሮች<br>• አወያዮች፣ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ሠራተኞች | ▪ የምክክር ጥራትን ማሳደግ<br>▪ የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ | ጥር 2015 ዓ.ም 6 ወር የሚፈጅ ፕሮጀክት | 3,000,000 | ▪ ለኢኮቴ ልማት በቂ በጀት ይመደባል፤<br>▪ የተለዩ የኢኮቴ መሠረተ ልማቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤ | ▪ ጥናቱ በወቅቱ መድረሱ፤<br>▪ ድረ ገጹን ወቅታዊ አለማድረግ፣ |
| 3.2 | የሶፍትዌርና አፕሊኬሽን ፕሮጀክት | የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ | የኢኮቴ ዳይሬክተር | " " " | ▪ የምክክር ጥራትን ማሳደግ | መጋቢት 2015 ዓ.ም **6 ወር የሚፈጅ ፕሮጀክት** | 10,000,000 | " " " | ▪ ጥናቱ በወቅቱ መድረሱ፤<br>▪ በቂ የአጠቃቀም ብቃት አለመፈጠር |
| 3.3 | የመረጃ ቋት ግንባታ ፕሮጀክት | የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ | የኢኮቴ ዳይሬክተር | " " " | ▪ የምክክር ተደራሽነትን ማሳደግ | ታህሳስ 2015 ዓ.ም 3 ወር የሚፈጅ ፕሮጀክት | 10,000,000 | " " " | ▪ ጥናቱ በወቅቱ መድረሱ፤<br>▪ የመረጃ ቋት የመጠቀም ብቃት አለመፈጠር፣ |
| 4. | የሥልጠናና የሰው ኃብት ልማት ፕሮግራም | የሴክሬታሪያት ፅ/ቤት ኃላፊ | የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር | • የሴክሬታሪያት ፅ/ቤት<br>• ኮሚሽነሮች<br>• የኮሚሽኑ አመራሮች<br>• ባለሙያዎች | የሠራተኛና ሥራ መሪዎች ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣ የኢኮቴ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ | 2016 ዓ.ም የ1 ዓመት ፕሮግራም | 6,000,000 | ለሥልጠና በቂ ሀብት ይመደባል፤ ትክክለኛ የሥልጠና አቅራቢዎች ይመደባሉ፤ | ▪ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ላይሆን መቻሉ፤<br>▪ በሥልጠና የተገኘ ክህሎት ተግባራዊ ላይሆን መቻሉ፣ |

| ተ/ቁ | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ | ባለድርሻ አካላት | በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ግቦች | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ወጪ በብር | ቁልፍ እሳቤዎችና ተግዳሮቶች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የተሳታፊዎች ክህሎት ማሳደግ፣ | | | | |
| 4.1 | የሠራተኛ ሥልጠና ፕሮጀክት | የሴክሬታሪያት ፅ/ቤት ኃላፊ | የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር | • የኮሚሺኑ አመራሮች<br>• የኮሚሺኑ ሠራተኞች | የሠራተኛ ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | 〃 〃 〃 | 1,000,000 | 〃 〃 〃 | ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ላይሆን መቻሉ፤ |
| 4.2 | የሥራ መሪዎች ሥልጠናና ልማት ፕሮጀክት | የሴክሬታሪያት ፅ/ቤት ኃላፊ | የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር | • የኮሚሽኑ አመራሮች፤<br>• ኮሚሽነሮች | የአመራር ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | 〃 〃 〃 | 2,000,000 | 〃 〃 〃 | ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ላይሆን መቻሉ፤ |
| 4.3 | የተሳታፊዎች፣ የአወያዮችና አመቻቾች ሥልጠና ፕሮጀክት | የተወከለ ኮሚሽነር | የኮሚሽኑ ሴክሬታሪያት | • ኮሚሽነሮች<br>• አወያዮችና አመቻቾች | የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ማሳደግ | 〃 〃 〃 | 3,000,000 | 〃 〃 〃 | ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ላይሆን መቻሉ፤ |
| 5. | የሀብት ማፈላለግ ፕሮጀክት | የኮሚሽነሮች ም/ቤት ሰብሳቢ | የተወከለ ኮሚሽነር | • ኮሚሽነሮች<br>• የልማት አጋሮች | የፋይናስ አቅርቦትን ማሳደግ | ሰኔ 2015 ዓ.ም | 500,000 | • የልማት አጋሮች በቂ ሀብት ይመድባሉ፤ | ▪ በምክክር ሂደቱ ኃብት የመደቡ አካላት ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፤<br>▪ ቃል የተገባው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ላይገኝ ይችላል፤ |
| 6. | የቤንችማርኪንግና የዕውቀት ሥራ አመራር ፕሮጀክት | የኮሚሺነሮች ም/ቤት ሰብሳቢ | የተወከለ ኮሚሽነር | • ኮሚሽነሮች | የአመራር ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | 〃 〃 〃<br>የሦስት ወር ፕሮጀክት | 3,000,000 | • በቂ ልምድና ዕውቀት ያለባቸው ሀገራት ይለያሉ፤<br>• ለቤንችማርኪንግ በቂ ሀብት ይመደባል፤ | ▪ የተገኘውን ልምድ በወቅቱ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ |

| ተ/ቁ | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ | ባለድርሻ አካላት | በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ግቦች | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ወጪ በብር | ቁልፍ እሳቤዎችና ተግዳሮቶች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የምክክር ሂደት ጥራትን ማሳደግ | | | | ተግባራዊ ላይሆን ይችላል፤ |
| 7. | የስትራቴጂያዊ አጋርነት ስትራቴጂና አሠራር ዝግጅት ፕሮጀክት | የኮሚሽነሮች ም/ቤት ሰብሳቢ | የተወከለ ኮሚሽነር | • ኮሚሽነሮች<br>• የልማት አጋሮች | የፋይናስ አቅርቦትን ማሳደግ<br>ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ<br>የስትራቴጂያዊ አጋርነት ውጤታማነትን ማሳደግ | ሰኔ 2015 ዓ.ም<br>የ3 ወር ፕሮጀክት | 500,000 | • የልማት አጋሮች ለትብብር ፈቃደኛነት ያሳያሉ፤ | የተዘጋጀው ስትራቴጂ በታቀደው ልክ አለመተግበር፤ |
| 8. | የኢንፎርሜሽን ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ስትራቴጂና ዕቅድ ፕሮጀክት | የኮሚሽነሮች ም/ቤት ሰብሳቢ | የተወከለ ኮሚሽነር | • ኮሚሽነሮች<br>• አወያዮችና አመቻቾች<br>• ሚዲያዎች<br>• ህዝቡ /ዜጋው | የህዝቡን ግንዛቤን ማሳደግ፣<br>የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፣ | መስከረም 2015 ዓ.ም<br>የ2 ወር ፕሮጀክት | 750,000 | • በኮሚኒኬሽን ስትራቴጂና ዕቅድ መመራት ውጤታማ ኮሙኒኬሽን ለማከናወን ይስችላል፤ | የተዘጋጀው ስትራቴጂና ዕቅድ በታቀደው ልክ አለመተግበር፤ |
| 9. | ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ድጋፍ ፕሮጀክት | የኮሚሽነሮች ም/ቤት ሰብሳቢ | የተወከለ ኮሚሽነር | •ኮሚሽነሮች<br>•የሲቪክ ማኅበራት | ተሳትፎን ማሳደግ | 〃 〃 〃<br>የአንድ ወር ፕሮጀክት | 400,000 | ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ደጋፍ ቢሰጣቸው ተሳትፏቸው ይጨምራል፤ | የአገልግሎት መመሪያዎች በአግባቡ ተግባራዊ የማይሆኑበት ጊዜ አለ፤ |
| **አጠቃላይ የፕሮጀክት በጀት** | | | | | | | 42,650,000 | | |